## ምዕራፍ ፡ ፪፶፮ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፡ ስዊድን ።

፩ ፤ የስዊድን ፡ ግዛቶች ፡ ኖርዌንና ፡ የላፕላንድን ፡ እኩሌታ ፡ ጨምሮ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ አገሮች ፡ በሰሜን ፡ ወገን ፡ ከአርክቲክ ፡ ውቅያኖስ ፤ በምሥራቅ ፡ ወገን ፡ ከላፕላንድ ፡ ከቦታኒያና ፡ ከቦልቲክ ፡ ባሕር ፤ ከደቡብ ፡ ወገን ፡ በቦልቲክ ፡ ካቴጋት ፡ እስካጀር ፡ ራክ ፤ በምዕራብ ፡ ወገን ፡ ከአትላንቲክ ፡ ባሕር ፡ ይዋሰናል ።

፪ ፤ ስዊድን ፡ ብርዳምና ፡ ተራራ ፡ የበዛበት ፡ አገር ፡ ነው ። በብረት ፡ ረገድ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ነው ። ከዚሁ ፡ ከስዊድን ፡ አገር ፡ ወደዚህ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ብረት ፡ ይመጣል ። ሕዝቡ ፡ ሠራተኞችና ፡ ጕበዞች ፤ ልበ ፡ ቅኖችና ፡ ነጻ ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ። ከባላገሮቹ ፡ የሚበዙት ፡ በወተት ፤ በአይብ ፤ በዓሣ ፡ ብቻ ፡ ይኖራሉ ። የክረምት ፡ ልብሳቸው ፡ የለዘበ ፡ ጠጕርና ፡ የበግ ፡ አጐዛ ፡ ነው ።

፫ ፤ ስዊድኖች ፡ ንቁዎች ፡ ናቸው ። ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ መሥራት ፡ ይችላሉ ። ረዥም ፡ ክረምታቸው ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ያበባውን ፡ ወራት ፡ ለማክበር ፡ ሲሉ ፡ ምሰሶ ፡ ተክለው ፡ ዙሪያውን ፡ እየዞሩ ፡ ይጨፍራሉ ። አገራቸውን ፡ ይወዳሉ ። ከዓለም ፡ ያማረው ፡ ክፍል ፡ ስዊድን ፡ በመሆኑ ፡ አምነው ፡ ይኖራሉ ።

፬ ፤ ምንም ፡ ልብሳቸው ፡ የበግ ፡ ለምድ ፡ ቢሆን ፡ መኖሪያ ፡ ቤታቸውም ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ቢሆን ፡ እነርሱ ፡ እጅግ ፡ ሥልጡኖች ፡ ናቸው ። ከነገርኋችሁ ፡ ነገሥታትና ፡ መኳንንት ፡ ይልቅ ፡ እነዚህ ፡ የተወደዱ ፡ ከበሬታ ፡ የሚገባቸው ፡ አስተዋዮች ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ።

፭ ፤ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ዋሱና ፡ ተያገዥ ፡ መልካም ፡ ጠባይና ፡ በጎ ፡ አካሄድ ፡ መሆናቸውን ፡ ሳልነግራችሁ ፤ ጊዜ ፡ አጥቼ ፡ ቈይቻለሁ ። ይልቁንም ፡ ለነዚህ ፡ ሀብታሞች ፡ ላልሆኑ ፡ ሰዎች ፡ አስፈላጎች ፡ ናቸው ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ባለጠጎችንና ፡ ከበርቴዎችን ፤ ኵራትና ፡ ትዕቢት ፡ ያፍናቸዋል ። ይህ ፡ የማይገባ ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ይንቃቸዋል ። ከብረታቸውም ፡ በዙሪያቸው ፡ አቈላማጮችን ፡ ያስነሣባቸዋል ።

፮ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ትሑታን ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ከመውደድ ፤ ከትሕትና ፤ ከበጎ ፡ አካሄድ ፤ ከጨዋነት ፡ የተነሣ ፡ የመጣላቸውን ፡ ደስታ ፡ ሊወረውሩት ፡ አይችሉም ።

፯ ፤ ስዊድኖች ፡ ጥንተ ፡ ታሪካቸው ፡ እጅግም ፡ አይታወቅ ። ጥንት ፡ በደንማርክ ፡ ይገዙ ፡ ነበር ። በ፲፫፻፺፯ ፡ ደንማርክ ፤ ስዊድን ፤ ኖርዌ ፡ ማርጋሬት ፡ በተባለች ፡ በደንማርክ ፡ ንግሥት ፡ ይገዙ ፡ ነበር ።

፰ ፤ በ፲፭፻፲፰ ፡ ክርስቲያን ፡ የተባለ ፡ የደንማርክ ፡ ንጉሥ ፡ ፪ኛ ፡ የስዊድንን ፡ አማካሪዎች ፡ በአስቶክሆልም ፡ ከተማ ፡ ስላ ፡ አሳረዳቸው ፡ ጉስታቩስ ፡ ቫሳ ፡ የተባለ ፡ ያንዱ ፡ አማካሪ ፡ ልጅ ፡ ስዊድኖች ፡ በደንማርክ ፡ ላይ ፡ እንዲያምጹ ፡ አስነሣቸው ።

፱ ፤ የዴንማርክ ፡ ንጉሥ ፡ የተነሣውን ፡ ዐመጽ ፡ ጸጥ ፡ ለማድረግ ፡ ጦር ፡ ቢሰድ ፡ የዴንማርክ ፡ ወታደሮች ፡ የተሳፈሩባቸው ፡ መርከቦች ፡ በስዊድን ፡ ጠረፍ ፡ ሲደርሱ ፡ ከበረዶ ፡ ተጋጭተው ፡ ስለ ፡ ቆሙ ፡ የስዊድን ፡ ባላገሮች ፡ ወታደሮቹን ፡ ከጠረፋቸው ፡ አባረሩና ፡ መርከቦቹን ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉዋቸው ።

፲ ፤ ጉስታፉስ ፡ ቫሳ ፡ እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ አገሩን ፡ ነጻ ፡ ስላወጣ ፡ ወዲያው ፡ ለንጉሥነት ፡ ተመረጠ ። ከርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ በስዊድን ፡ የነገሠው ፡ ሊነገርለትም ፡ የሚገባው ፡ ጉስታፍ ፡ አዶልፍ ፡ የተባለው ፡ ነው ። እርሱም ፡ በ፲፮፻፲፩ ፡ በተወለደ ፡ በ፲፮ ፡ ዓመቱ ፡ ነገሠ ።

፲፩ ፤ ይህ ፡ ንጉሥ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ጀግና ፡ ነው ። ስለ ፡ ፕሮቴስታንቶች ፡ ተዋግቶ ፡ ድል ፡ ያደረገ ፡ ነው ። በጀርመን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ወገን ፡ ሁኖ ፡ የሚዋጋውን ፡ የታወቀውን ፡ ጀኔራል ድል ፡ አድርጎታል ። በ፲፮፻፴፪ ፡ በሉትዝን ፡ ሲዋጋ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ሳለ ፡ በድሉ ፡ መጨረሻ ፡ ከዚያው ፡ ከጦርነቱ ፡ ሞተ ።

፲፪ ፤ ጉስታፍ ፡ አዶልፍ ፡ የሞተው ፡ ክርስቲና ፡ የተባለች ፡ የ፮ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ትቶ ፡ ነው ። የታወቀች ፡ መታሰቢያ ፡ ትሆናለች ፡ ተብላ ፡ ትታሰብ ፡ ነበርና ፡ ትምህርት ፡ እንድታገኝ ፡ ታላቅ ፡ ጥንቃቄ ፡ ተደረገላት ። ነገር ፡ ግን ፡ መልካም ፡ ሴት ፤ ወይም ፡ መልካም ፡ ንግሥት ፡ አልሆነችም ።

፲፫ ፤ ንግሥት ፡ ክርስቲና ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ ከገዛች ፡ በኋላ ፡ ደካማ ፡ ስለ ፡ ሆነች ፡ የመንግሥቱን ፡ ጉዳይ ፡ ለማከናወን ፡ አልቻለችም ። ስለዚህ ፡ ከስዊድን ፡ ይልቅ ፡ ለመኖሪያዋ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛትን ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ለመፈለግ ፡ ዙፋንዋን ፡ ትታ ፡ ሄደች ።

፲፬ ፤ በግዛታቸው ፡ ውስጥ ፡ ጠባይዋ ፡ የተበላሸ ፡ እንደዚች ፡ ያለች ፡ ሴት ፡ በመገኘትዋ ፡ ለመላው ፡ የኤውሮጳ ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ ኀፍረት ፡ ሆነባቸው ። በመጨረሻውም ፡ የካቶሊክን ፡ ሃይማኖት ፡ ተቀበለችና ፡ ጳጳስ ፡ በሮማ ፡ እንድትኖር ፡ ፈቀዱላት ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ የስዊድን ፡ ግዛት ፡ የትኛውን ፡ አገር ፡ ጨምሮ ፡ ነው ፡ ?

፪ ፤ ስዊድን ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ አገር ፡ ነው ፡ ? ሕዝቡስ ፡ ?

፫ ፤ ስዊድኖች ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ፡ ?

፬ ፤ አለባበሳቸው ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ጠባይና ፡ አካሄድስ ፡ ?

፭ ፤ መልካም ፡ ልማድ ፡ አላቸውን ፡ ? ብልጽግናና ፡ ሀብትስ ፡ ?

፮ ፤ ሕዝቡ ፡ ትሕትና ፡ የለበሱ ፡ ናቸውን ፡ ? የስዊድን ፡ ታሪክ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? በ፲፫፻፹፮ ፡ ማን ፡ ይገዛቸው ፡ ነበር ፡ ? በ፲፭፻፳፫ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ? ጉስታቩስ ፡ ቫሳ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፱ ፡ ንጉሡ ፡ እንደምን ፡ ሆነ ፡ ? መርከቦቹስ ፡ ?

፲ ፤ ጉስታቩስ ፡ ቫሳ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ? በ፲፮፻፲፩ ፡ የስዊድን ፡ ንጉሥ ፡ ማን ፡ ነበር ፡ ?

፲፩ ፤ ጉስታቩ ፡ አዶልፍ ፡ ማነው ፡ ? በየትኛው ፡ ውጊያ ፡ ሞተ ፡ ?

፲፪ ፤ ስለ ፡ ንግሥት ፡ ክርስቲና ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ ?

፲፬ ፤ ወዴት ፡ ለመኖር ፡ ተፈቀደላት ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፻፺፯ ፡ ኤውሮጳ ።

### ፲፪ኛ ካርልና ፡ ሠራዊቱ ።

፩ ፤ ዝናው ፡ በመላ ፡ ዓለም ፡ የታወቀ ፡ እጅግ ፡ ስሙ ፡ ጥሩ ፡ የነበረ ፡ የስዌድን ፡ ንጉሥ ፡ ካርል ፡ ፲፪ኛ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን የደግኖችን ፡ ታሪክ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በመስማት ፡ ያከማችኋልና ፡ የካርልን ፡ ታሪክ ፡ በጭሩ ፡ እንግራችኋለሁ ።

፪ ፤ ዕድሜው ፡ ፲፭ ፡ ዓመት ፡ ሲሆን ፡ በ፲፮፻፺፯ ፡ ነገሠ ። ከሕፃንነት ፡ ጀምሮ ፡ ትልቅ ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፡ ከወታደርነት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አይመኝም ፡ ነበር ። ፲፯ ፡ ዓመት ፡ ሲሆነው ፡ የረሺያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤ የፖላንድ ፡ ንጉሥ ፤ የደንማርክ ፡ ንጉሥ ፤ ሆኑና ፡ ጦርነት ፡ ገጠሙት ።

፫ ፤ መጀመሪያ ፡ ሁሉንም ፡ ካርል ፡ መታቸው ። የጥይት ፡ አረር ፡ በጆሮው ፡ አጠገብ ፡ ስታፍዋጭ ፡ የሰማ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከደስታው ፡ የተነሣ ፡ ይህች ፡ የኔ ፡ ሙዚቃ ፡ ነች ፡ ይል ፡ ነበር ። በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሙዚቃ ፡ የሚሉ ፡ ነገር ፡ አይመኝም ፡ ነበር ።

፬ ፤ የጥይት ፡ አረር ፡ ስታፍዋጭ ፡ ደስ ፡ የሚለው ፡ ንጉሥ ፡ ያላቸው ፡ ሕዝብ ፡ እጅግ ፡ የሚያሳዝኑ ፡ ናቸው ። ካርል ፡ ፲፪ኛ ፡ ለመላው ፡ ኤውሮጳ ፡ እንደ ፡ መግረፊያ ፡ ጅራፍ ፡ ያለ ፡ ነበር ። ይልቁንም ፡ ስገዛ ፡ ዜጋው ፡ ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ ለሚገኘው ፡ ለመልካም ፡ ጥቅም ፡ ሳይጓጓ ፡ ለሙዋጋቱ ፡ ብቻ ፡ ሲል ፡ ጦርነትን ፡ ይወድ ፡ ነበር ።

፭ ፤ ካርል ፡ መጀመሪያ ፡ እንደ ፡ ነገሠ ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ ሁለጊዜ ፡ ይቀናው ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በ፲፯፻፱ ፡ ክዛር ፡ የረሺያው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፑልቶዋ ፡ ላይ ፡ በተዋጉ ፡ ጊዜ ፡ ድል ፡ አደረገውና ፡ ካርል ፡ ወደ ፡ ቱርክ ፡ ሸሽቶ ፡ አመለጠ ።

፮ ፤ በዚያው ፡ አገር ፡ ፭ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ተቀምጦ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ወደጎና ፡ ሳይመለስ ፡ አይቀርም ። ስለ ፡ መንግሥቱ ፡ ጥንቃቄ ፡ ያለው ፡ አይመስልም ። ስዌድኖች ፡ ንጉሣቸው ፡ ወሄደበት ፡ እልም ፡ ብሎ ፡ ሲጠፋባቸው ፡ ጊዜ ፡ እንዴት ፡ እናድርግ ፡ ብለው ፡ ቢልኩበት ፡ ካርል ፡ ይኸ ፡ ይግዛችሁ ፡ አለና ፡ አንዱን ፡ ጫማውን ፡ አውልቆ ፡ ሰደደላቸው ።

፯ ፤ በመጨረሻው ፡ በ፲፯፻፲፬ ፡ የቱርክን ፡ አገር ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ስዌድን ፡ ተመለሰ ። የመጀመሪያ ፡ ሥራውም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ጦርነት ፡ ማድረግ ፡ ሆነ ። ነገረ ፡ ግን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የጦርነት ፡ ሥራ ፡ ሊፈጸም ፡ ተቃርቦ ፡ ነበር ።

፰ ፤ አንድ ፡ ቀን ፡ ሌሊት ፡ በኖርዌ ፡ ምሽጉን ፡ ለማየት ፡ ከወታደሮቹ ፡ ቀድሞ ፡ ሲሄድ ፡ አንድ ፡ መድፍ ፡ ተተኩሰና ፡ ራሱን ፡ መትቶት ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የታጠቀውን ፡ ሰይፍ ፡ ከሰገባው ፡ እስከ ፡ መኻከሉ ፡ ድረስ ፡ መዝዞት ፡ ተገኘ ። አንዳንዶች ፡ ግን ፡ ታርዶ ፡ ነው ፡ የተገኘው ፡ እያሉ ፡ አበርትተው ፡ ይናገራሉ ። ካርል ፡ ፲፪ኛ ፡ ጀግና ፡ ወይም ፡ እብድ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ይቸገራሉ ።

፱ ፤ ከወራሾቹ ፡ አንዱን ፡ ጉስታቩስ ፡ ፫ኛን ፡ እንዳይታወቅ ፡ ተሰውሮ ፡ ሳለ ፡ በ፲፯
፻፺፪ ፡ በጥይት ፡ ገደሉት ። ጉስታቩስ ፡ ፬ኛ ፡ የተባለው ፡ ዜጎቹ ፡ ዙፋኑን ፡ ለመተው ፡
እንዲያስገድዱት ፡ አደረገ ። ይኸም ፡ የሆነው ፡ በ፲፰፻-፱ ፡ ነው ።

፲ ፤ ቀጥሎ ፡ የነገሠው ፡ ካርል ፡ ፲፫ኛ ፡ ነው ። በ፲፰፻፲ ፡ ስዌድኖች ፡ ቤርናዶት ፡
የተባለውን ፡ አንድ ፡ የፈረንሳይ ፡ ጀኔራል ፡ የስዌድን ፡ መንግሥት ፡ ዐልጋ ፡ ወራሽ ፡
እንዲሆን ፡ መረጡት ። ፲፰፻፲፰ ፡ ካርል ፡ ፲፫ኛ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ቤርናዶት ፡ ዙፋ
ኑን ፡ ወረሰ ።

፲፩ ፤ በ፲፰፻፵፬ ፡ ቤርናዶት ፡ ሞተ ። ልጁ ፡ አስካር ፡ ፩ኛ ፡ እስከ ፡ ሞተበት ፡ ዘመን ፡
እስከ ፡ ፲፰፻፶፱ ፡ ነገሠና ፡ ልጁ ፡ ካርል ፡ ፲፭ኛ ፡ ወረሰው ። እርሱም ፡ በ፲፰፻፸፪ ፡
ሞተና ፡ ወንድሙ ፡ አስካር ፡ ፪ኛ ፡ በተራው ፡ ነገሠ ። የሕዝቡ ፡ ቍጥር ፡ ፭ ፡
ሚሊዮን ፡ ነው ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ከስዌድን ፡ ነገሥታት ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ የተባለ ፡ ማነው ፡ ?

፪ ፤ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነገሠ ፡ ? ሊወጋው ፡ የተነሣ ፡ ማነው ፡ ?

፫ ፤ ስለርሱ ፡ ምን ፡ አጭር ፡ ታሪክ ፡ ትናገራለህ ፡ ?

፬ ፤ መጀመሪያ ፡ እንደ ፡ ነገሠ ፡ ጥቂት ፡ ዓመታት ፡ ካርል ፡ ፲፪ኛ ፡ የተባለ ፡
እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ ?
የፑልቱዋ ፡ ጦርነት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነበር ፡ ?

፭ ፡ በቱርክ ፡ አገር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ተቀመጠ ፡ ?
ከስዌድኖች ፡ ተልከው ፡ ለመጡ ፡ መልክተኞች ፡ ምን ፡ መልስ ፡ መለሰላቸው ፡ ?

፮ ፤ ካርል ፡ ወደ ፡ ስዌድን ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተመለሰ ፡ ?
ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፯ ፡ አሟሟቱ ፡ እንደምንድነው ፡ ?
ስለ ፡ ካርልስ ፡ ፲፪ኛ ፡ ባለታሪኮች ፡ ምን ፡ ይላሉ ፡ ?

፰ ፤ ዙፋኑን ፡ ማን ፡ ወረሰው ፡ ?
ጉስታቩስ ፡ ፫ኛ ፡ የተባለ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ፡ ?
ጉስታቩስ ፡ ፬ኛ ፡ የተባለው ፡ ከዙፋኑ ፡ የተሻረው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

፱ ፤ ቀጥሎ ፡ ማን ፡ ነገሠ ፡ ?
የስዌድንን ፡ ዐልጋ ፡ ቤርናዶት ፡ የወረሰው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

፲ ፤ ቤርናዶት ፡ ማነው ፡ እርሱ ፡ ?
ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ማን ፡ ነገሠ ፡ ?

፲፩ ፤ የኋለኛው ፡ ንጉሥ ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ትናገራለህ ፡ ?
የሕዝቡ ፡ ብዛት ፡ ስንት ፡ ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፳፱ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፡ ላፕላንድ ፡ ኖርዌና ፡ ደንማርክ ።

፩ ፤ በኤውሮጳ ፡ ሰሜን ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ አገር ፡ ላፕላንድ ፡ ይባላል ። ይህንም ፡ አገር ፡ ስዌድኖችና ፡ ረሺያኖች ፡ ተካፍለውታል ። አገሩ ፡ በጣም ፡ ብርዳም ፡ ነው ። ብራንዴ ፡ የምንለው ፡ ሙቀት ፡ ያለው ፡ አረቄ ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ ሊረጋ ፡ ይችላል ። ላፕላንዶች ፡ ለጥቅማቸው ፡ በረዶውን ፡ የሚያቀል ጡበት ፡ መንገድ ፡ ያላቸው ፡ ይመስለኛል ።

፪ ፤ ስለ ፡ ላፕላንዶች ፡ አስቀድሜ ፡ ነግሬያችኋለሁ ። ወንዶቹ ፡ ቁመታቸው ፡ አራት ፡ ፊት ፡ ነው ። ሴቶቹ ፡ ቁመታቸው ፡ ከቤርሚል ፡ አይረዝምም ፤ እንደ ፡ ድኩላ ፡ የሚመስሉ ፡ ሬንዲር ፡ የሚሉዋቸው ፡ ሥጋቸው ፡ ለመብል ፤ ቆዳቸው ፡ ለልብስ ፡ የሚሆን ፡ እንስሶች ፡ አሉዋቸው ። ደግሞ ፡ ስለ ፡ ፈረስ ፡ ሆነው ፡ በጋሪ ፡ ሕዝቡን ፡ በበረዶ ፡ ላይ ፡ ይጐትታሉ ። ሕዝቡ ፡ ታሪክ ፡ ስለሌላቸው ፡ በዚህ ፡ ሊተረክላቸው ፡ ይገባል ።

፫ ፤ ኖርዌ ፡ አንድ ፡ ሰፊ ፡ አገር ፡ ነው ። በምሥራቅ ፡ ወገን ፡ ከስዌድን ፡ በምዕራብ ፡ ወገን ፡ ከአትላንቲክ ፡ ውቅያኖስ ፡ ይዋሰናል ፤ አገሩ ፡ ብርዳም ፤ ገላጣ ፡ ታርሶ ፡ የማያውቅ ፡ እዳሪ ፡ ነው ። ሕዝቡ ፡ ግን ፡ በምቾት ፡ ይኖሩበታል ። ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ላሞች ፡ አሉዋቸው ። ከነዚሁ ፡ በዓለም ፡ የታወቀ ፡ የተሻለ ፡ ቅቤ ፡ ያወጣሉ ።

፬ ፤ ታላቁ ፡ ከተማ ፡ ቤርጂን ፡ ይባላል ። ሠላሳ ፡ ሺሕ ፡ ባላገሮች ፡ አሉበት ። ቤቶቻቸው ፡ ትንንሾች ፡ ናቸው ። የተሠሩት ፡ ከዕንጨት ፡ ብቻ ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እሳት ፡ ያጠቃቸዋል ። ስለዚህ ፡ ወፍራም ፡ ከት ፡ ተጐንበው ፡ ሌሊት ፡ በዋናው ፡ ጐዳና ፡ እየተዛወሩ ፡ የሚመለከቱ ፡ ዘበኞች ፡ አሉ ። እግዚአብሔር ፡ መልካሚቱን ፡ ከተማችንን ፡ ቤርጂንን ፡ ይጠብቃት ፡ እያሉ ፡ በየሰዓቱ ፡ ይጮኻሉ ።

፭ ፤ ኖርዌ ፡ ጥንት ፡ ዘመን ፡ ባላገሮቹ ፡ ያልሠለጠኑ ፡ መርከቦችን ፡ የሚያስጨንቁ ፡ ባለጌ ፡ ነገድ ፡ ነበሩ ። አሁንም ፡ ቢሆን ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ የባሕር ፡ ቀማኞች ፡ ከመኻከላቸው ፡ አይታጡም ። በኋላ ፡ የኖርዌ ፡ ሰዎች ፡ እየሄዱ ፡ መኖሪያ ፡ ያደረጓትን ፡ አይስላንድ ፡ የተባለችውን ፡ ሰፊ ፡ ደሴት ፡ በ፰፻፷ ፡ ያገኘ ፡ ናይድ ፡ የተባለ ፡ የባሕር ፡ ወንበዴ ፡ ነው ።

፮ ፤ በ፲፻፳ ፡ ካኑት ፡ የተባለ ፡ የደንማርክ ፡ ንጉሥ ፡ ኖርዌዎችን ፡ ድል ፡ አድርጓቸው ፡ ሳለ ፡ ከ፯ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ነጻነታቸውን ፡ አገኙ ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ኖርዌ ፡ በገዛ ፡ ራስዋ ፡ ንጉሥ ፡ ተገዝታ ፡ ኖረች ። በ፲፰፻፯ ፡ ከደንማርክ ፡ ጋር ፡ ስምምነት ፡ አደረጉና ፡ ወደ ፡ ስዌድን ፡ እስኪያልፍ ፡ እስከ ፡ ፲፰፻፺፯ ፡ ድረስ ፡ አንድነት ፡ ሁነው ፡ ነበር ።

፯ ፤ ደንማርክ ፡ በስዌድንና ፡ በጀርመን ፡ መኻከል ፡ ያለች ፡ ትንሽ ፡ መንግሥት ፡ ናት ፡ አገሪቱ ፡ አባጣ ፡ ጐባጣ ፡ የሌለባት ፡ ትክክል ፡ ሜዳ ፡ ሁና ፡ ዙሪያዋን ፡ በባሕር ፡ የተከበበች ፡ ናት ። ከተማዪቱ ፡ ኮፐንሀግን ፡ መቶ ፡ ፹ ፡ ሺሕ ፡ ባለገሮች ፡ አሉባት ። የሕዝቡ ፡ ብዛት ፡ ሁለት ፡ ሚሊዮን ፡ ናቸው ። ደንማርኮች ፡ በ፪ቱ ፡ በደንማርክና ፡ በኖርዌ ፡ ቋንቋ ፡ ይናገራሉ ።

፰ ፤ እነዚህ ፡ ሦስት ፡ የደንማርክ ፤ መንግሥታት ፡ ኖርዌና ፡ ስዌድን ፡ ቀድሞ ፡ ዘመን ፡ እስካንዲኒቪያን ፡ ይባሉ ፡ ነበር ። ቀድሞ ፡ ዘመን ፡ እነዚህን ፡ አገሮች ፡ ነገደ ፡ ፊንላድና ፡ ነገደ ፡ ጀርመን ፡ ይዘዋቸው ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ጎቶች ፡ መጡና ፡ እነዚሁን ፡ አገሮች ፡ ድል ፡ አደረጉዋቸው ። መሪያቸው ፡ ኦዲን ፡ ይባል ፡ ነበር ። ስለ ፡ ርሱም ፡ እጅግ ፡ የሚያስገርም ፡ ታሪክ ፡ ይነገርለታል ። በነዚህ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ባሉት ፡ ነገድ ፡ ዘንድ እንደ ፡ ጁፒትር ፡ ያመልኩት ፡ ነበር ፡ ይላሉ ። የመጀመርያው ፡ የደንማርክ ፡ ንጉሥ ፡ የኦዲን ፡ ልጅ ፡ እስኪአልድ ፡ ይባላል ።

፱ ፤ ቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ደንማርክ ፡ የምናውቀው ፤ ሕዝቡ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍራ ፡ የተጠራቀሙ ፡ ወንበዶች ፡ መሆናቸውን ፡ ነው ። በሰሜን ፡ ኤውሮጳ ፡ ያሉት ፡ ነገዶች ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ቀማኞች ፡ ይቈጥሩዋቸው ፡ ነበር ።

፲ ፤ እነዚህ ፡ እንደ ፡ ፈቀዱ ፡ ይዘርፉ ፡ የነበሩ ፡ ቀማኞች ፡ በትንሽ ፡ መርከባቸው ፡ ሆነው ፡ ወጡና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮችን ፡ እያሸነፉ ፡ ያዙ ። ከነርሱም ፡ ተከፍለው ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ተቀመጡ ። እኩሉም ፡ ኖርማንዲ ፡ በሚሉት ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፤ እኩሉም ፡ ወደ እስጴንና ፡ ወደ ፡ ኢጣልያ ፡ ደረሱ ።

፲፩ ፤ በ፱፻፳ ፡ አያሎች ፡ የሚሆኑ ፡ ነገደ ፡ ዳኒሽ ፡ ባንድነት ፡ ሆኑና ፡ አንድ ፡ መንግሥት ፡ አቆሙ ፡ በ፲፻፲፮ ፡ ካኑት ፡ እንግሊዝን ፡ ድል ፡ አደረገና ፡ የእስኮትላንድን ፡ እኩሌታ ፡ እጁ ፡ አደረገ ። በ፲፻፴ ፡ ኖርዌ ፡ ተገዛለት ። ከርሱ ፡ በኋላ ፡ በደንማርክ ፡ አያሎች ፡ ገዦች ፡ እየተነሡ ፡ ብዙ ፡ ጦርነት ፡ አድርገዋል ። የኋለኛው ፡ ገዢ ፡ ለአገሩ ፡ ተከላካይ አንድ ፡ ብቻውን ፡ እርሱ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፡ የመጡበትን ፡ ፕሩሲያኖችንና ፡ አስትሪያኖችን ፡ ስላልቻለ ፡ ድል ፡ አደረጉት ። ጀግኖቹ ፡ ደንማርኮች ፡ ስለ ፡ ተሸነፉ ፡ ለጀርመን ፡ ተጨማሪ ፡ ለሆኑት ፡ ለሹልስዊግና ፡ ሆልስትን ፤ መገዛት ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው ። በኋላ ፡ ግን ፡ የፕሩሲያ ፡ መንግሥት ፡ ክፍል ፡ ሆነው ፡ ነበር ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ላፕላንድ ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ ? አየሩ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፪ ፤ ላፕላንዶች ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ? ሬንዲር ፡ የሚሉዋቸው ፡ እንስሶች ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ? ታሪካቸውስ ፡ ?

፫ ፤ ኖርዌ በወዴት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ? አገሩ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ? ሕዝቡስ ፡ ቅቤውስ ፡ ?

፬ ፤ ቢርጂን ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ነው ፣ ? የሕዝብ ፣ ብዛትስ ፣ ? ቤቶች ፣ እን ዴት ፣ ያሉ ፣ ናቸው ፣ ? ሁልጊዜ ፣ የእሳት ፣ አደጋ ፣ ይነሣልን ፣ ? ጠባቂ ፣ ዘበኛ ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ነው ፣ ?

፭ ፤ ጥንት ፣ በኖርዌ ፣ ሰው ፣ እንደምን ፣ ገባ ፣ ? በ፰፻፰ ፣ ምን ፣ ተደረገ ፣ ?

፮ ፤ ኖርዌ ፣ የተሸነፈው ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ? ያሸነፈውስ ፣ ማነው ፣ ? ነጻ ፣ የወጣው ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ? በ፲ሮ፻፺፯ ፣ ምን ፣ ሆኖ ፣ ነበር ፣ ? በ፲፰፻፲፬ ፣ ምን ፣ ሆነ ፣ ?

፯ ፤ ደንማርክ ፣ ወዴት ፣ ነው ፣ ? እንዴት ፣ ያለ ፣ አገር ፣ ነው ፣ ? ኮፐንሀ ግን ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ከተማ ፣ ነው ፣ ? የሕዝብዋ ፣ ብዛትስ ፣ ? የደን ማርክ ፣ መንግሥት ፣ ሕዝብ ፣ ብዛት ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ? በኖርዌና ፣ በደነማርክ ፣ ምን ፣ ቋንቋ ፣ ይናገራሉ ፣ ? ቋንቋቸው ፣ ምንድነው ፣ ?

፰ ፤ እስካንዲናቪያ ፣ የተባሉ ፣ ሦስት ፣ አገሮች ፣ እነማን ፣ ናቸው ፣ ?
እነዚህኑ ፣ አገሮች ፣ ማን ፣ ይዘዋቸዋል ፣ ?
እነዚህን ፣ ነገዶች ፣ ማን ፣ መራቸው ፣ ?
መጀመርያ ፣ በደንማርክ ፣ የነገሠው ፣ ማነው ፣ ?
ጥንት ፣ ዘመን ፣ ደንማርክ ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ አገር ፣ ነበር ፣ ?
ኖርማን ፣ የተባሉት ፣ ሕዝብ ፣ እነማን ፣ ናቸው ፣ ?

፲ ፤ እነዚህ ፣ ቀማኞች ፣ እንዴት ፣ አደረጉ ፣ ? መኖርያቸውን ፣ ወዴት ፣ አደረጉ ፣ ?

፲፩ ፤ በ፱፻፹ ፣ ምን ፣ ሆነ ፣ ? ካኑት ፣ ምን ፣ አደረገ ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ?
የደንማርክ ፣ ታሪክ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?
የመጨረሻው ፣ ጦርነት ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ? ከዚያ ፣ የተነሣ ፣ ምንና ፣ ምን ፣ ሆነ ፣ ?

## ምዕራፍ ፣ ፲፺፱ ።

### ስለ ፣ ብዙዎች ፣ መንግሥት ፣ አጭር ፣ ማስታወቂያ ።

፩ ፤ አያሎች ፣ የኤውሮጳ ፣ አገሮች ፣ ስላ ፣ አሉ ፣ የነዚህን ፣ የያንዳንዳቸውን ፣ ታሪክ ፣ እ'ለየሁ ፣ ልነግራችሁ ፣ አልችልም ። ያንዳንዱቹ ፣ ታሪክ ፣ ከሌላው ፣ መንግሥት ጋር ፣ ተቀላቅሎ ፣ ስላ ፣ ተነገረ ። የቀረው ፣ ባጭሩ ፣ ባንድ ፣ ምዕራፍ ፣ ይነገራል ።

፪ ፤ ጊዜ ፣ ባገኝስ ፣ ስለ ፣ ሆላንድ ፣ ረጅም ፣ ታሪክ ፣ ብተርክ ፣ በወደድሁ ፣ ነበር ። ይህ ፣ አገር ፣ አንድ ፣ ጊዜ ፣ በወሃ ፣ ተሸፍኖ ፣ የነበረ ፣ አገር ፣ ነው ። አሁን ፣ ግን ፣ ዙሪያውን ፣ በሰፊው ፣ ሁኖ ፣ ተገንብቶአል ። የሆላንድ ፣ ሕዝብ ፣ ደች ፣ ይባላሉ ። አጥበቀው ፣ ሲጃራ ፣ ጠጪዎች ፣ መሆናቸው ፣ በዓለም ፣ ታውቆአል ። ሕዝቡ ፣ ሠራተኞች ፣ ናቸው ። ደኃና ፣ ምስኪን ፣ ሆኖ ፣ ሳላ ፣ በአገሩ ፣ በጥሩ ፣ ቤት ፣ የሚኖር ፣ እንደ ፣ ሆላንድ ፣ ሰው ፣ አይገኝም ። በዋናው ፣ ከተማ ፣ በአ ምስተርዳም ፣ ከ፪፻ ፣ ሺሕ ፣ የሚበልጡ ፣ ባላገሮች ፣ ይኖሩበታል ።

፫ ፤ ቤልጊዩም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ አገር ፡ ነው ። ዋና ፡ ከተማው ፡ ብሩስልስ ፡ ያማረ ፡ ከተማ ፡ ነው ። ሊዎፓልድ ፡ አንደኛ ፡ በተባለው ፡ በቀድሞው ፡ ንጉሥ ትጋትና ፡ ጥንቃቄ ፤ ንግድና ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ እያለ፡ሄዶ፡ ነበር ። አገሩ ፡ በጣም ፡ ያማረ ፡ ነው ። ባንዳንድ ፡ ስፍራም ፡ የተወደደ ፡ ነው ።

፬ ፤ ኒድርላንድ ፡ ወይም ፡ ሆላንድ ፡ ቤልጊዩም ፡ ቢባል ፡ ቀድሞ ፡ እነዚህ፡ሁሉ፡ አንድ ፡ አገር ፡ ነበሩ ። መላው ፡ ግዛቱ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ከሰሜን ፡ ባሕር ፡ ይዋሰናል ። በምሥራቅ ፡ ወገን ፡ ከጀርመን ፤ በደቡብ ፡ ወገን ፡ ከፈረንሳይ ፤ በምዕራብ ፡ ወገን ፡ ከእንግሊዝ ፡ ካናልና ፡ ከሰሜን ፡ ባሕር ፡ ይዋሰናል ። እነዚህ ፡ ግዛቶች ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ዘመን ፡ ለሮም ፤ ቀጥሎም ፡ ለጀርመን ፤ በመጨረሻ ፡ ለእስጳንያ ፡ ተገዝተው ፡ ነበሩ ።

፭ ፤ በ፲፭፻፹፩ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ያሉት ፡ ሰባቱ ፡ አህጉር ፡ በፊልጵ ፡ በእስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ ሸፈቱና ፡ በራሳቸው፡ የሬፑብሊክ፡መንግሥት፡ስለ፡አቆሙ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ሆላንድ ፡ ተባለ ። ባ፲፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት፡ኀይለኞች፡ሆነው፡ ይልቁንም ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ኀይላቸው ፡ ብርቱ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መርከባቸው ፡ ከእንግሊዝ ፡ መርከቦች ፡ ጋር ፡ እየተከራከረች ፡ ትመታቸው ፡ ነበረች ።

፮ ፤ የቀሩት ፡ የኒድርላንድ ፡ አገሮች ፡ አያሌ ፡ ዘመን ፡ ለኦስትርያ ፡ ተገዝተው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። በ፲፰፻፲ ፡ ሆላንድ ፡ ከፈረንሳይ ፡ ጋር ፡ ተቀላቀለ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሆላንድና ፡ ዝቅ ፡ ያሉት ፡ አገሮች ፡ በኋላ ፡ የተለያየ ፡ መንግሥት ፡ አቆሙ ። በ፲፰፻፴ ፡ ዐመፅ ፡ ተነሣና ፡ የደቡብ፡አገሮች፡የቤልጅግን ፡ መንግሥት ፡ አበረቱ ።

፯ ፤ ፖላንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የኤውሮጳ ፡ ነገድ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን፡እንደዚህ ፡ ሁኖ ፡ አልቈየም ። በሰሜንና ፡ በምሥራቅ ፡ ወገን ፡ ከረሺያ ፡ ግዛት ፤ ከደቡብ ፡ ወገን ፡ ከኢስትር ፡ ወንዝ ፤ በምዕራብ ፡ ወገን ፡ ከፕሩሲያ ፡ ይዋሰናል ። በ፲፯፻ ፸፪ ፡ የረሺያ ፡ የፕሩሲያና ፡ የኦስትሪያ ፡ ገዦች ፡ ፖላንድን ፡ ያዙዋት ። ከግዛትዋም ፡ የሚበልጠውን ፡ ክፍል ፡ ለራሳቸው ፡ ተከፋፈሉት ። በ፲፯፻፺፭ ፡ የቀረውን ፡ ጠቅልለው ፡ ያዙ ። ባላገሮቹም ፡ ስለ ፡ ነጻነታቸው ፡ ታገሉ ። ዳሩ ፡ ግን፡ ትግላቸው ፡ ከንቱ ፡ ሆነ ። ዋናው ፡ ከተማ ፡ ዋርሳዎ ፡ ይባላል ። አገሩ ፡ በብዙ ፡ ስፍራ ፡ ለም ፡ ነውና ፡ እህል ፡ ይሆናል ። ለስዌድንና፡ለሆላንድ ፡ ብዙ ፡ ሲሳይ ፡ ይሰጣል ። ለከብት ፡ ሰፊ ፡ መሰማሪያ ፡ አለው ።

፰ ፤ ስለ ፡ ኢጣሊያ ፡ አውራጃዎች ፡ ፊት ፡ አጭር ፡ አሳብ ፡ ሰጥቻችሁ ፡ ነበር ። እንደ ፡ ገና ፡ ጥቂት ፡ መልሼ ፡ ብነግራችሁ ፡ አይከፋም ። እንደምታውቁት ፡ የቬኒስ ፡ ሬፑብሊክ ፡ የተመሠረተው ፡ በ፭ኛው ፡ መቶ ዓመት ፡ ነው ። ፊት ፡ የታወቁት ፡ በቬኒስ ፡ ባሕር ፡ አጠገብ ፡ ጥቂቶች ፡ ረግረግ ፡ የሆኑ ፡ ደሴቶች ፡ ብቻ፡ ነበሩ ። በኋላ ፡ ሰፋ ፡ ያለው ፡ ግዛት ፡ ለመንግሥቱ ፡ ተጨመረለት ።

፱ ፤ ቬኒስ ፡ ሰፊ ፡ ንግድ ፡ ነበራት ፤ በ፲፫ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የሬፑብሊክ፡ መንግሥት ፡ በጣም ፡ ኀይል ፡ አግኝቶ ፡ ስለ፡ነበር ፤ በታላቅ ፡ ሥርዓት ፡ ጋብቻ፡ ባሕርን ፡ እንደሚስት ፡ ለማጨት ፡ ለብልሁ ፡ ለቬኒስ ፡ ገዢ ፡ ልማድ ፡ ነበረው ።

ምንም ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ፈራርሳ ፡ ብትታይ ፡ እስካሁን ፡ ለመንገደኞች ፡ መደነቂያ ፡ ናት ። ስለ፡ሆነ ፡ ኢጣሊያ ፡ ከምታገኘው ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ፈጽሞ ፡ ተስፋ ፡ አልጠፋም ። አሁን ፡ እንኳ ፡ ጥቂት ፡ ይታያል ።

፲ ፤ በኢጣሊያ ፡ ሰሜን ፡ ምዕራብ ፡ ያለች ፡ ጄኒዋ ፡ ቀድሞ ፡ ቬኒስ ፡ ግዛትዋ ፡ ሳለ ፡ ኀይል ፡ አልነበራትም ። በ፲፰፻፲፭ ፡ ለሳርዲኒያ ፡ ግዛት ፡ ተጨመረች ። ሳርዲኒያ ፡ በሜዲቴራኒያ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ያለች ፡ ደሴትና ፡ ከ፲፯፻፳ ፡ ወዲህ፡ መንግሥት ፡ የሆነች ፡ ናት ።

፲፩ ፤ የቀድሞ ፡ የናፕል ፡ መንግሥት ፡ መቸውንም ፡ የሁለቱ ፡ ሲሲሊዎች ፡ መንግሥት ፡ ይባል ፡ ነበር ። ግዛቱ ፡ ከሲሲሊ ፡ ደሴትና ፡ በዙሪያው ፡ ካሉት ፡ ከትንንሾች ፡ ደሴቶች ፡ ሌላ ፡ የኢጣልያንን ፡ ደቡብ ፡ ሁሉ ፡ ይጨምራል ። የቀድሞ ፡ የናፕል ፡ ነገሥታት ፡ ከእስጳንያ ፡ የመጡ ፡ ናቸው ።

፲፪ ፤ በ፲፰፻፰ ፡ ንጉሡ ፡ ናፖሊዮን ፡ የናፕልን ፡ መንግሥት ፡ ዮአኪን፡ሙራት ፡ ለተባለ ፡ ላንድ ፡ ለስመ ፡ ጥሩ ፡ ጄኔራሉ ፡ ሰጠው ። ይህም ፡ የአንድ ፡ ምግብ ፡ አሰናጂ ፡ ልጅ ፡ ነበር ። ንጉሥ ፡ ዮአኪን ፡ በ፲፰፻፲፭ ፡ በጥይት ፡ ሞተና፡ሁለቱም ፡ ሲሲሊዎች ፡ ፌርዲናንድ ፡ ለተባለ ፡ ለቀድሞው ፡ ንጉሥ ፡ ተመለሱለት ። አሁንም፡ ግንኙነት ፡ ካላቸው ፡ ከኢጣሊያ ፡ አውራጃዎች ፡ አንዱ ፡ እርሱ ፡ ነው ።

## ጥያቄ ።

፪ ፡ ሆላንድ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ አገር ፡ ነው ፡ ? ሕዝቡስ ፡ ? በአምስተርዳም፡የሕዝብ ፡ ብዛት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡?

፫ ፤ ቤልጊዩም ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? የቀድሞው ፡ ንጉሥ ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ?

፬ ፤ ሆላንድና ፡ ቤልጊዩም ፡ እንዴት፡ናቸው፡? ግዛቱ፡እንደምን፡ተወሰኖአል፡? በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘመን ፡ ለማን ፡ ተገዝቶአል ፡?

፭ ፤ በ፲፰፻፴፩ ፡ ምን ፡ ሆነ፡? ሆላንድ ፡ እጅግ ፡ ኀይል ፡ ተሰምቶት ፡ የነበረ ፡ መቸ ፡ ነው፡?

፮ ፤ የቀሩት፡የኒድርላንድ፡አውራጆች፡እንድምን፡ሆኑ፡? በ፲፰፻፲፡ምን ፡ ሆነ፡ ? በ፲፰፻፴ ፡ ፖላንድ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
ወሰኑና ፡ ዳርቻው ስ፡? በ፲፯፻፸፪ ፡ ምን ፡ ሆነ፡ ? በ፲፯፻፺፭ ፡ ፖላንዶች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ፡?

፯ ፤ ቬኒስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፱ ፤ ኀይል ፡ የነበረው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው፡? በየዓመቱ ፡ የሚደረገው ፡ በዓል ፡ መቼ፡ነው፡? አሁን ፡ ቬኒስ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፲ ፤ ጄኖዋ፡እንዴት፡ነው፡? ሳርዲኒያ፡መንግሥት፡የሆነው፡ከመቼ፡ወዲህ፡ነው፡?

፲፩ ፤ በጠቅላላው ፡ የናፕል ፡ መንግሥት ፡ ምን ፡ ይባል ፡ ኖሮአል ፡ ?

፲፪ ፤ ናፖሊዮን ፡ እንዴት ፡ ሆነ፡? ንጉሥ ፡ ዮአኪን ፡ እንዴት፡ሆነ፡? ንጉሥ ፡ ፌርዲናንድ ፡ እንደምን ፡ ሆነ ፡?

## ምዕራፍ ፣ ፫ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፡ ታላቁ ፡ ብሪታኒያና ፡ ስለ ፤ አየርላንድ ፡ መንግሥት ።

፩ ፤ በኤውሮጳ፡እጅግ ደስ ፡ ወደሚያሰኘው ፡ አገር፡አሁን፡መጥቻለሁ ። ይኸውም ፡ አገር ፡ ከእስያ ፡ ወይም ፡ ከአፍሪካ ፡ እንዲያውም ፡ በኤውሮጳ ፡ካሉት ፡ አገሮች ፡ ይልቅ ፡ ብዙ ፡ ምቾትና ፡ ብዙ ፡ ዕውቀት ፡ ታላቅ ፡ ሥልጣኔና ፡ እውነተኛ ፡ ሃይማኖት ፡ ያለበት ፡ አገር ፡ ነው ።

፪ ፤ የታላቁ ፡ ብሪታኒያና ፡ የአየርላንድ ፡ መንግሥት ፡ ሲባል ፡ እንግላንድ ፤ ዌልስ ፤ እስኮትላንድ ፤ አየርላንድ ፤ በንድነት ፡ ሆነው ፡ ነው ። የፊተኞቹ ፡ ሦስቱ ፡ አገሮች በእንግሊዝ፡ደሴት ፡ ላይ፡ናቸው ። ይኸውም፡ደሴት፡ያለው፡በኤውሮጳ ፡ ምዕራብ ፡ ጠረፍ ፡ ነው ። ከፈረንሳይ ፡ የሚለይበት ፡ በእንግሊዝ ፡ ካናል ፡ ነው ። ይኸም ፡ ካናል ፡ እጠባቡ ፡ ላይ ፡ ፳፩ ፡ ማይል ፡ ስፋት ፡ አለው ። አየርላንድ፡ ከታላቁ ፡ ብሪቴን ፡ ምዕራብ ፡ ወገን ፡ ነው ። ፳፡ማይል ፡ ይርቃል ። ስለ ፡ ሆነ ፡ ግማሹ ፡ ለእስኮትላንድ ፡ የቀረበ ፡ ነው ።

፫ ፤ እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ ደሴቶች፡በስፋት ፡ ጠባብ ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ፴፫ ፡ ሚሊዮን ፡ ባላገሮች ፡ ይኖሩባቸዋል ። ከዚህ ፡ በቀር ፡ ደግሞ ፡ መንግሥቱ ፡ በልዩ ፡ ልዩ፡ ቦታ ፡ የቅኝ ፡ አገር ፡ አለው ። በአሜሪካ ፤ በአፍሪካ ፤ በእስያ ፤ መንግሥቱ፡ በብዙ ፡ ሚሊዮን፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ይገዛል ። ታላቁ ፡ ብሪታኒያ ፡ በዓለም ፡ ላይ፡ ሀብታምና ፡ ኀይለኛ ፡ መንግሥት ፡ ተብሎ ፡ ይታሰባል ።

፬ ፤ እንግሊዝ ፡ አያሌ ቶች ፡ የሚታዩና ፡ ያማሩ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቶች ፡ አሉት ። ደግሞ ፡ እንግሊዝ ፡ እጅግ ፡ የበበሩና ፡ የተሟላላቸው፡ ከበርቴዎች ፤ በሕዝቡ፡ ዐይን ፡ የተወደዱና ፡ ክቡራን ፡ ሰዎች ፡ ላገራቸው ፡ በጣም ፡ ቅናትና ፡ ያገር ፡ ፍቅር ፡ የመላባቸው ፡ መኳንንት ፡ አሉት ።

፭ ፤ ታላላቅ ፡ ከተሞች ። ባሉበት ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ታላቅ ፡ ድኅነትና ፡ ችግር ፡ አይታጣም ። በእንግሊዝ ከተሞች ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ እንደዚህ፡አይሆንም ። ነገር ፡ ግን ፡ ለድኆች ፡ እየተባለ ፡ ለበጎነት ፡ ሥራ ፡ በተሰበሰበው ፡ ገንዘብ ፡ የድኆችን ፡ ችግር ፡ ያቀሉላቸዋል ። በየትም ፡ ቢሆን ፡ የድኆችን ፡ ችግር ፡ ለማቃለል ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ የሚሰጥ ፡ አገር ፡ አይገኝም ።

### ጥያቄ ።

፩ ፤ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ በኤውሮጳ ፡ የታወቀ ፡ አገር ፡ ማነው ፡ ?

፪ ፤ የታላቁ ፡ ብሪታኒያና ፡ የአየርላንድ ፡ መንግሥት ፡ የሚባሉት ፡ ማንና፡ ማን፡ናቸው፡ ?
የታላቁ ፡ ብሪታኒያ ፡ ደሴት ፡ እንዴት ፡ ነው፡? የብሪቲሽ ፡ የውሃ፡መንገድ ፡ እንዴት ፡ ነው፡ ? አየርላንድስ፡ ?

፫ ፤ የታላቁ ፡ ብሪታኒያ ፡ ሕዝብ ፡ ብዛት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ፡ ? የአየርላንድስ ፡ ?
፬ ፤ መንግሥቱ ፡ እንደምንድነው ፡ ? ከቡራኑሳ ፡ ?
፭ ፤ ድኀነት ፡ በእንግሊንድ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ስለ ፡ እንግላንድ ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ ?
ሎንዶን ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ ?
ከዚህ ፡ የሚከተሉት ፡ ስፍራዎች ፡ ከሎንዶን ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ ናቸው ፡ ?
ማንቼስትር ፡ ? በርሚንግሀም ፡ ? ሼፊልድ ፡ ? ኤድንቡርግ ? ዱብሊን ፡ ? ዌልስ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፺፩ ፡ ኤውሮጳ ።

ስለ ፡ ሎንዶንና ፡ ዐሳ ፡ ሌሎች ፡ የእንግሊዝ ፡ ከተሞች ፡ ስለ ፡ ዌልስና እስኮትላንድ ስለ አየርላንድም ።

፩ ፤ በኤውሮጳ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ ሰፊ ፡ ከተማ ፡ የተባለ ፡ ሎንዶን ፡ ነው ። በከተማው ፡ ዙሪያ ፡ ያሉትን ፡ ጨምሮ ፡ ከ፫ ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ የሚበዙ አሉበት ። በከተማውም ፡ መኻል ፡ ለመኻል ፡ የሚሄድ ፡ ቴምስ ፡ የሚሉት ፡ ወንዝ ፡ አለ ። በዕንጨትና ፡ በብረት ፡ የተሠሩ ፡ ያማሩ ፡ ድልድዮች ፡ ይታያሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሎንዶን ፡ ከተማው ፡ በሚያምሩ ፡ አገሮች ፡ እንጂ ፡ ዙሪያውን ፡ በቅጥር ፡ አል ተከበበም ።

፪ ፤ ሎንዶን ፡ እጅግ ፡ ያማሩ ፡ ቤቶችና ፡ ሕንፃዎች ፡ አሉዋት ። ከነዚህ ፡ መኻከል ፡ ዌስትሚኒስትር ፡ አቤ ፡ ስለሚባለው ፡ አመለክታለሁ ። ይህም ፡ የጥንት ፡ የኀቶች ፡ አሠራር ፡ ዐይነት ፡ ነው ። አያሎች ፡ የእንግሊዝ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውድ ፡ የሚጭኑት ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ነው ። አያሎችም ፡ የሚፈተኑ ፡ በዚህ ፡ ነው ። ክሪስቶፌር ፡ የሠራው ፡ የቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይህም ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ በዓለም ፡ የታወቀ ፡ የጵሮቴስታንቶች ፡ የአምልኮት ፡ ስፍራ ፡ ነው ። በኪንግሀም ፡ የተባለው ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ነገሥታቱ ፡ የሚኖሩበት ፡ ነው ።

፫ ፤ የቀድሞው ፡ ምሽግ ፡ ታላቁ ፡ ግንብ ፡ የመንግሥት ፡ ወህኒ ፡ ያለበት ፤ የደቡብ ፡ ኪንሲንግቶን ፡ ሙዜውም ፡ ብዙ ፡ ጠቀሜታ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ የተሰበሰበበት ፤ አዲሱ ፡ የፓርላሜቱ ፡ ቤት ፡ ዋናው ፡ በሎንዶን ፡ የታወቀው ፡ ሕንፃ ፡ የእንግሊዝ ፡ ሙዜውም ፡ ሮያል ፡ ኤክስቼንጅ ፡ ጊልድሆልና ፡ አልቤርትሆል ፡ ያሉበት ፡ ነው ።

፬ ፤ ደግሞ ፡ በሎንዶን ፡ ያማሩ ፡ አታክልቶች ፡ አሉ ። ከነዚህ ፡ የታወቁት ፡ ዋኖቹ ፡ ሀይድፓርክ ፤ ግሪንፓርክ ፤ ሲንት ፡ ጂምስ ፡ ፓርክ ፤ ሬጂንት ፡ ፓርክ ፤ ቪክቶሪያ ፡ ፓርክ ፡ ናቸው ። ወደ ፡ ደቡብና ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ለሕዝብ ፡ መመላለሻ ፡ በመሆኑ ፡ ቴምስ ፡ ሎንዶንን ፡ ለማሻሻል ፡ ታላቅ ፡ ረዳት ፡ ሆነ ።

፭ ፤ ማንቸስትር ፡ እጅግ ፡ ሰፊ ፡ ከተማ ፡ ነው ፡ ለመላው ፡ ዓለም ፡ ከጥጥ ፡ የሚሠራውን ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ የሚያዘጋጁበት ፡ ስፍራ ፡ ነው ። በርሚንግሀም ፡ ጠመንጃ ፤ ሽጉጥ ፡ ጐራዴ ፤ ብረታ ብረት ፡ የሚሠራበት ፡ ስፍራ ፡ ነው ። ሸፊልድ ፡ ካራ ፤ ሹካ ፤ መቀስ ፤ አያል ፡ መሣሪያ ፡ በያይነቱ ፡ ከጥሩ ፡ ብረት ፡ የተሠራ ፡ ለመርከብ ፡ የሚሆን ፡ የብረት ፡ ልብስ ፡ የሚሠራበት ፡ ስፍራ ፡ ነው ።

፮ ፤ ዌልስ ፡ ተራራ ፡ የበዛበት ፡ በእንግሊዝ ፡ ምዕራብ ፡ ያለው ፡ አገር ነው ። ከሕዝቡ ፡ የሚበዙት ፡ ማንም ፡ የማይሰማውንና ፡ ሊያስተውለው ፡ የማይችለውን ፡ የዌልስን ፡ ቋንቋ ፡ ይናገራሉ ። ሕዝቡ ፤ አጥብቀው ፡ ሠራተኞች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ በምቾት ፡ መልካም ፡ ኑሮ ፡ ይኖራሉ ። ተራሮቻቸው ፡ የድንጋይ ፡ ከሰል ፤ ቆርቆሮ ፤ ብረት ፤ መዳብና ፡ እስሌት ፡ (ታቡላ ፡ ) ይገኝባቸዋል ።

፯ ፤ እስኮትላንድ ፡ ተራራ ፡ የበዛበት ፡ አገር ፡ ነው ። አየሩ ፡ ተእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ይልቅ ፡ ይበርዳል ። በእስኮትላንድ ፡ ያማሩ ፡ ሐይቆች ፡ አሉበት ።

፰ ፤ የእስኮትላንድ ፡ ዋናው ፡ ከተማ ፡ ኤድንቡርግ ፡ ይባላል ። በመኻከሉ ፡ እጅግ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ሕንፃዎች ፡ ተሠርተዋል ። ከዚህ ፡ በቀር ፡ በእስኮትላንድ ፡ ሌሎች ፡ ያማሩ ፡ ከተሞች ፡ አሉበት ። ግላስኮ ፡ የሚሉት ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ እደ ፡ ጥበብ ፡ የሚከናወንበት ፡ ስፍራ ፡ ነው ።

፱ ፤ አየርላንድ ፡ ብሩህ ፡ የሆነ ፡ ለምለም ፡ ደሴት ፡ ነው ። ሰባት ፡ ሚሊዮን ፡ ባላገሮች ፡ አሉበት ። የነዚህ ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ፡ የሚኖሩ ፡ አይሪሾች ፡ አገር ፡ ነው ። ከነዚህ ፡ ብዙዎቹ ፡ እየተሰደዱ ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ። በአገራቸው ፡ ሁለመናው ፡ ተከናውኖላቸው ፡ ኖሮ ፡ ቢሆን ፡ አይሰደዱም ፤ ነበር ። እንደ ፡ እውነቱ ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ አየርላንዶች ፡ የሚሰደዱበት ፡ ምክንያት ፡ አገራቸው ፡ በአገዛዝ ፡ መጥፎና ፡ ክፉ ፡ በመሆኑ ፡ ከሕዝቡ ፡ የሚበዙት ፡ ወደ ፡ መከራና ፡ ወደ ፡ ድኅነት ፡ ስለ ፡ ወደቁ ፡ ነው ። በዛሬው ፡ አገዛዝ ፡ ግን ፡ የባላገሮቹ ፡ ሁኔታ ፡ በጣም ፡ ተሻሽሎአል ።

፲ ፤ በቤታቸውም ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ በውጭ ፡ አይሪሾች ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኙ ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ። ንቁዎችና ፡ ሰውን ፡ ማስተናገድ ፡ የሚያውቁ ፡ ናቸው ። በተወደደ ፡ ሁኔታቸውና ፡ በብሩህ ፡ ገጽ ፤ የደስታ ፡ መልክ ፡ በማሳየት ፤ ቍጡውን ፡ አለስልሰው ፡ በትዕግሥታቸው ፡ የሚያሸንፉ ፡ ይመስላሉ ።

፲፩ ፤ የአየርላንድ ፡ ዋናው ፡ ከተማ ፡ ዱብሊን ፡ ይባላል ። ጐዳናው ፡ መልካም ፡ ሆኖ ፡ የተሠራ ፡ ነው ። ሊፌ ፡ በተባለው ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ተሠርቶአል ። የአየርላንድ ፡ ሕዝብ ፡ ከአምስት ፡ ሚሊዮን ፡ በላይ ፡ ናቸው ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ የሎንዶን ፡ ሕዝብ ፡ ብዛት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ቴምስ ፡ ምንድነው ፡ ? በሎንዶን ፡ ዙሪያ ፡ ያሉ ፡ አገሮችስ ፡ ?
፪—፫ በሎንዶን ፡ ተሚታዩት ፡ ስለ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ቤቶች ፡ ተናገር ።
፬ ፤ ዋናው ፡ አታክልት ፡ ማን ፡ ይባላል ፡ ? በሎንዶን ፡ የተሻሻለው ፡ ምንድነው ፡ ?
፭ ፤ ማንቸስትር ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? በርሚንግሀምስ ፡ ? ፌልድስ ፡ ?
፮ ፤ ዌልስ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ? ተራራውስ ፡ ?
፯ ፤ እስኮትላንድ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ አገር ፡ ነው ፡ ?
፰ ፡ ኤድንቡርግርስ ፡ ? ግላስኮና ፡ አየርላንድ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ? አገዛዙስ?
፱ ፤ የአየርላንድ ፡ ሕዝብ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?
፲ ፤ ዱብሊን ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፭ ፡ ኤውሮጳ ።

### ድሩኢድስ በላ ፡ ተባሉ ፡ የእንግሊዝ ፡ የጥንት ፡ ሕዝብ ።

፩ ፤ ጥንት ፡ ዘመን ፡ በመጀመሪያ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ነገዶች ፡ ከጎል ፡ መጥተው ፡ በታላቅ ፡ ብሪታኒያና ፡ በአየርላንድ ፡ የሰፈሩ ፡ ይመስላል ። እነዚህም ፡ ጌልስ ፡ ወይም ፡ ኬልት ፡ ይባላሉ ። ዘራቸው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በአየርላንድና ፡ በዌልስ ፡ በእስኮትላንድም ፡ ይገኛል ። ከነዚህም ፡ አያሎች ፡ በጎሎች ፡ ወይም ፡ በኬልቶች ፡ ቋንቋ ፡ ይናገራሉ ።

፪ ፤ እነዚህ ፡ ደሴቶች ፡ እስከ ፡ ጁሊውስ ፡ ቄሣር ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ እጅግም ፡ አልታወቁም ፡ ነበር ። ፶፭ ፡ ከልደተ ፡ ክስቶስ ፡ በፊት ፡ ቄሣር ፡ እንግሊዝን ፡ በወረራት ፡ ጊዜ ፡ አገሩ ፡ ብሪታኒያ ፡ ወይም ፡ ብሪቴን ፡ ይባል ፡ ነበር ። አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ የሚኖሩበት ፡ ነው ። ከነርሱ ፡ እኩሌቶቹ ፡ ልብሳቸው ፡ የአውሬ ፡ ቆዳ ፡ ነበር ። እኩሌቶቹም ፡ ፈጽሞ ፡ ያለ ፡ ልብስ ፡ ዕርቃናቸውን ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። እንደ ፡ አሜሪካን ፡ ሀንዶች ፡ አድርገው ፡ አካላታቸውን ፡ ይነቀሳሉ ። የጦር ፡ መሣሪያቸው ፡ ዱላ ፤ ጦር ፤ ጐራዴ ፤ ነው ። ሮማውያን ፡ በወረሩዋቸው ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ይከላከላሉ ።

፫ ፤ የጥንቱ ፡ ብሪቶንስ ፡ የሚባሉ ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ እንደ ፡ ሰሜን ፡ ኤውሮጳ ፡ ነገድ ፡ ጣዖት ፡ ያመልኩ ፡ ነበር ። ካህናተ ፡ ጣዖት ፡ ድሩኢድስ ፡ ይባላሉ ። ለጣዖቱ ፡ በሚያገለግሉበት ፡ ስፍራ ፡ ዙሪያውን ፡ የድንጋይ ፡ ምሰሶ ፡ ያቆማሉ ። ያለውም ፡ በውጭ ፡ ከሜዳ ፡ ላይ ፡ ነው ። ስለ ፡ መሠዊያ ፡ ብለው ፡ አንድ ፡ ሰፊ ፡ ድንጋይ ፡ በመኻከል ፡ ያኖራሉ ። በዚያ ፡ ላይ ፡ ለመሥዋዕት ፡ የሚታረደውን ፡ ሰው ፡ ያቀርባሉ ። ያንዱ ፡ መከነ ፡ ጣዖት ፡ ፍራሽ ፤ እስቶንሂጅ ፡ በሚሉት ፡ ስፍራ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ይኖራል ። እጅግም ፡ ያስገርማል ።

፬ ፤ ድሩኢዶች ፡ ኦክ ፡ የሚሉትን ፡ ዛፍ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ነገር ፡ ያስቡታል ። በኦክ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ የሚበቅለውን ፡ ተቀጽላ ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ ጥቅም ፡ ያደርጉታል ። ተቀጽላው ፡ በቅሉበት ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ከንፉ ፡ በተንሰራፋው ፡ ኦክ ፡ በታች ፡ ከጥላው ፡ ታላቅ ፡ ግብር ፡ ያደርጋሉ ።

፭ ፤ ብሪቶኖች ፡ የሮማውያንን ፡ ኀይል ፡ እንዲቃወሙ ፡ ድሩኢዶች ፡ አነሳሡዋቸውና ፡ አጥብቀው ፡ ተዋጉ ። ከልደተ ፡ ክርስቶስ ፡ በኋላ ፡ ፷ ዓመት ፡ እስኪሆን ፡ አገሩ ፡ ፈጽሞ ፡ ለሮም ፡ አልተገዛም ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ ሱቶኒውስ ፡ የተባለ ፡ የሮም ፡ ጀኔራል ፡ ተነሣና ፡ የጣዖቱን ፡ ዐጸድ ፡ ሁሉ ፡ ቈረጠና ፡ ቤተ ፡ ጣዖቱንም ፡ ከአፈረሰው ፡ በኋላ ፡ ሮማውያንን ፡ ሊያቃጥሉበት ፡ ባነደዱት ፡ እሳት ፡ ድሩኢድስ ፡ የተባሉትን ፡ ካህናተ ፡ ጣዖት ፡ አግብቶ ፡ አቃጠላቸው ።

፮ ፤ በሰሜን ፡ እስኮትላንድ ፡ ደሴት ፡ የሚኖሩት ፡ ሕዝብ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በማንም ፡ ያልተሸነፉ ፡ ንዴት ፡ ያላቸው ፡ ጀግኖች ፡ ናቸው ። ወደ ፡ ብሪታንያ ፡ ገብተው ፡ እንዳይወሩ ፤ ሮማውያን ፡ ታይን ፡ ከሚባለው ፡ ወንዝ ፡ ጀምረው ፡ ዙሪያውን ፡ የሚከላከሉበት ፡ ግንብ ፡ ሠሩ ።

፯ ፤ ብሪታኒያዎችም ፡ ተልደተ ፡ ክርስቶስ ፡ በኋላ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ለሮማውያን ፡ እየተገዙ ፡ በጸጥታ ፡ ቈዩ ። በዚሁ ፡ በተገዙበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ የሮማውያንን ፡ ጠባይና ፡ ልማድ ፡ ተቀብለው ፡ ኖሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ የሮም ፡ መንግሥት ፡ እያደር ፡ እየደከመ ፡ ሄደና ፡ ንጉሣቸው ፡ ቫሌንቲኒያን ፡ የተባለ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱን ፡ ጥርግርግ ፡ አድርጎ ፡ ከብሪታኒያ ፡ ሄደ ።

፰ ፤ የሮም ፡ ጭፍሮች ፡ አገሩን ፡ ለቀው ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ የብሪታንያ ፡ ባላገሮች ፡ ጦርነት ፡ የማያውቁ ፡ ነበሩና ፡ የእስኮትላንድን ፡ ሰዎች ፡ ተዋግተው ፡ የማይመልሱ ፡ መሆናቸውን ፡ ስለ ፡ ተረዱት ፤ ረዳት ፡ የሚሆኑዋቸው ፡ ሳክሶንና ፡ እንግሊዝ ፡ የተባሉ ፡ ነገድ ፡ እዲመጡላቸው ፡ ጀርመንን ፡ ለመኑ ።

፱ ፤ እነዚህም ፡ እስኮትላንዶችን ፡ ወግተው ፡ እያባረሩ ፡ በደሴታቸው ፡ እንዲወሰኑ ፡ አደረጉዋቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ወደ ፡ ጀርመን ፡ በመመለስ ፡ ፈንታ ፡ ብሪታኒያ ፡ ላኛ ፡ ይገባናል ፡ ብለው ፡ በኀይል ፡ አንፈራጠው ፡ ተቀመጡ ። አገሩን ፡ ከሰባት ፡ ከፍለው ፡ የሳክሶን ፡ ሰባት ፡ መንግሥታት ፡ አሰኙት ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ጎሎች ፡ ወይም ፡ ኬልቶች ፡ የተባሉ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ፡ ?
፪ ፤ እንግላንድን ፡ ቄሣር ፡ የወረረው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
ታላቁ ፡ ብሪታኒያ ፡ ምን ፡ ይባል ፡ ነበር ፡ ? ሕዝቡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?
፫ ፤ የጥንት ፡ ብሪቶናች ፡ ሃይማኖትስ ፡ ? ድሩኢድስ ፡ የተባሉት ፡ ምንድናቸው ፡ ? ቤተ ፡ ጣዖታቸው ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?
፬—፭ ፤ ድሩኢድስ ፡ በተባሉት ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ አክ ፡ የሚሉት ፡ ዛፍ ፡ ምን ፡ ይታሰብ ፡ ነበር ፡ ? ሱቶኒውስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፮ ፤ እስኮትላንዶች ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ? ሮማውያን ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?
፯ ፤ ሮም ፡ ብሪቲንን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ገዛው ፡ ? የቫሌንቲኒያን ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፰ ፤ ብሪቶን ፡ በእስኮት ፡ ላይ ፡ ሲነሣ ፡ የማን ፡ ረዳትነት ፡ ፈለገ ፡ ?
፱ ፤ እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ነገዶች ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?
ብሪቶንስ ፡ እንዴት ፡ ተከፋፈሉ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፪ኛ ፡ ኤውሮጳ ።

### ሳክሶንና ፡ የደንማርክ ፡ ነገሥታት ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ።

፩ ፤ በ፰፻-፯ ፡ ከልደት ፡ በኋላ ፡ እነዚህ ፡ የሳክሶን ፡ ሰባት ፡ መንግሥታት ፡ የተባሉ ፡ በኤግበርት ፡ መሪነት ፡ በአንድነት ፡ ገጠሙ ። ስለዚህ ፡ እርሱ ፡ የመጀመሪያው ፡ የእንግሊዝ ፡ ንጉሥ ፡ ሆነ ።

፪ ፤ ኤግበርት ፡ የእንግሊዝ ፡ ተወላጅ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ተምሮ ፡ በሻርለማኝ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ያደገ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ስለ ፡ ዚህ ፡ ከሳክ

ሰን ፡ ገዢዎች ፡ ይልቅ ፡ እርሱ ፡ በጣም ፡ የተማረ ፡ የሠለጠነና ፡ የሕዘበ፡ሰው ፡ ነበር ። በኤግበርት፡ዘመን ፡ ደንማርኮች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የእንግሊዝን ፡ አገር ፡ እየ ወረሩ ፡ ያስቸግሩ ፡ ነበር ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በገሩ ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ይጋልቡ በት ፡ ነበሩ ።

፫ ፤ በ፰፻፸፰፡የነገሠ፡አልፍሬድ ፡ በባሕርና ፡ በየብስ ፡ ፶፮ ፡ ጊዜ፡ተዋግቶዋቸዋል። ባንድ ፡ ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ ተሰውሮ ፡ ሰው ፡ ሳያውቀው ፡ በገና ፡ ደርዳሪ ፡ መስሎ ፡ ወደ፡ደንማርኮች ፡ ሰፈር ፡ ገባና ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ መርምሮ ከተረዳው ፡ በኋላ ፡ በሰፈራቸው ላይ ፡ አደጋ ፡ ለመጣል ፡ አስቦ ፡ ወደ ሰዎቹ ፡ ተመልሶ ፡ ሄደና ፡ የጦር ፡ መሪ ፡ ሆኖ ፡ በደንማርኮች ፡ ላይ ፡ ወደቀባቸውና ፡ ፈጽሞ ፡ አጠፋቸው ።

፬ ፤ ይህም ፡ ንጉሥ ፡ ታላቁ ፡ አልፍሬድ ፡ ተባለ ። ካያሉት ፡ ነገሥታት ፡ ይልቅ፡ ለርሱ ፡ ታላቅ ፡ ማዕርግ ፡ የተገባው ፡ ሰው ፡ ነበር ። ሕግንና ፡ ፍርድን ፡ እንደ ሚገባ ፡ አደረገ ። እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ የአክስፎርድን ፡ ዩኒቬርስቲ ፡ መሠረተ ። እርሱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ሲሆን ፡ ደንማርኮች ፡ እንደ፡ገና፡ከእን ግሊዞች ፡ ጋር ፡ ጦርነት ፡ አበቀሉ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሚቃወማቸው ፡ አልፍ ሬድ ፡ ስለ ፡ ሌለ ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ሦስቱ ፡ የደንማርክ ፡ ነገሥታት ፡ እየተ ከታተሉ ፡ አገሩን ፡ ገዝተውታል ።

፭ ፤ ከነርሱ ፡ አንዱ ፡ ካኑት ፡ ታላቁ ፡ የተባለው ፡ ነው ። እርሱም፡አንድ፡የባሕር ፡ ቀማኛ ፤ ወይም ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ እንደሚሉት ፡ የባሕር ፡ ንጉሥ ፡ ይባል ፡ ነበር ። አንድ ፡ ቀን ፡ ከመኳንንቱ ፡ ጋር፡በባሕር ፡ ዳር፡ ሲሄድ ፡ ሳለ፡መቸም ፡ የባ ሕር ፡ ንጉሥ ፡ ተብሎአልና ፡ በሕርም ፡ ማዕበልም ፡ ለቃልህ ፡ ይታዘዛሉ፡ይሉት ፡ ነበር ።

፮ ፤ ካኑት ፡ ይህ ፡ የማይደረግ ፡ ይመስላችኋልን ፡ ብሎ ፡ ቊልምጫቸውን ፡ ለማሳ ፈር ፡ የንጉሡን መቀመጫ ፡ ወንበር ፡ አምጥተው ፡ ከባሕሩ ፡ ዳር ፡ በአሸዋ ፡ ላይ ፡ እንዲያኖሩለት ፡ አዘዘ ። በወንበር ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ማዕበሉ ፡ በትረ ፡ መንግሥቱን ፡ ዘረጋና ፡ ትእዛዝ ፡ አደረገ ።

፯ ፤ "አንተ ፡ ማዕበል ፤ አንተ፡ባሕር ፡ ወደኋላህ ፡ ተመለስ፡እኔ ፡ ንጉሥህና፡ጌታህ ፡ ነኝ ። አንተ ፡ እረፋና ፡ ነጕድጓድ ፡ እንዴትስ ፡ በፊቴ ፡ ትደፍራለህ " እያለ ፡ ጮኸ ። ነገር፡ግን ፡ ባሕሩ ፡ በንጉሡና፡በመኳንንቱ ፡ ላይ ፡ ተንበጫርቆ ፡ መጥቶ ፡ ተከለበሰባቸው ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ አላፈረም ። የባሕሩ ፡ ሞገድ ፡ የንጉሡን ፡ መቀ መጫ ፡ ዘለለና ፡ ወደ ፡ ዳር ፡ ተወረወረ ። ቶሎ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ደረቅ ፡ ምድር፡ ባይፈተለኩ ፡ ቀርተው ፡ ኑረው፡ቢሆን፡ያን ፡ ጊዜውን፡ተግተውት፡ያርፉ ፡ ነበር ።

፰ ፤ በሺ ፡ ፵፩ ፡ ደንማርኮች ፡ ተእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ተባርረው ፡ ወጡና ፡ ኤድዋ ርድ ። የንፍስ ፡ አባት ፡ የተባለ ፡ ሌላ ፡ የሳክሶን ፡ ንጉሥ፡በዙፋኑ፡ተቀመጠበት ። በሺ ፡ ፷፮ ፡ ይህ ፡ ሲሞት ፡ ሀሮልድ ፡ የተባለ ፡ ክሳክሶን ፡ ነገሠ ።

፱ ፤ ነገር፡ግን ፡ ከሳክሶን ፡ ከነገሡት ፡ እርሱ ፡ መጨረሻ ፡ ሆነ ። እርሱ፡ከመንገሡ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ዊልየም ፡ የተባለ ፡ የኖርማንዲ ፡ ዱክ፡እንግሊዝን፡በ፷፡ሺሕ፡ ሰዎች ፡ ወረረና ፡ በሺ ፡ ፷፮ ፡ በፒብንሲ ፡ ጠረፍ ፡ ሲደርስ ፡ ከመርከብ ፡ ወረደ ።

፲ ፤ በኖርማንዶች ፡ ላይ ፡ የሳክሶንን ፡ ወታደሮች ፡ ሰደደባቸውና ፡ በሀስቲግም ፡ ላይ ፡ ተዋጋ ። ከጦርነቱ ፡ ውስጥ ፡ ሳለ ፡ አንዲት ፡ ፍላጻ ፡ በራስ ፡ ቍሩ ፡ ላይ ፡ ወጋችውና ፡ ወደ ፡ አንጐሉ ፡ ዘለቀች ። ድሉም ፡ ለኖርማንዲ ፡ ዱክ ፡ ሆነና ፡ የእንግሊዝ ፡ ንጉሥ ፡ ተባለ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ የእንግላንድ ፡ የመጀመሪያው ፡ ንጉሥ ፡ ማነው ? በእንዴት ፡ ያለ ፡ አገዛዝ ፡ ገዛ ፡ ?
፪ ፤ ኤግበርት ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ? ደንማርኮች፡እንዴት፡ ሆኑ ፡ ?
፫ ፤ አልፍሬድ ፡ በዙፋን፡የተቀመጠው ፡ ምን፡ጊዜ ፡ ነው፡? ምን ፡ አደረገ፡ ?
፬ ፤ ስለምን ፡ ታላቁ ፡ አልፍሬድ ፡ ተባለ ፡ ? ከርሱ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ ደንማርኮች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
፭.፮-፯ ፤ የከኑትን ፡ ታሪክ ፡ ተናገር ።
፰ ፤ ደንማርኮች ፡ ከእንግላንድ ፡ የወጡ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ በዙፋኑ ፡ ማን ፡ ተቀመጠበት ፡ ?
ሀሮልድ ፡ ንጉሥ ፡ የሆነው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
፱ ፤ አሁን ፡ እንግላንድን ፡ የወረረ ፡ ማነው ፡ ?
፲ ፤ ሀሮልድና ፡ ዊልየም ፡ የት ፡ ላይ ፡ ተዋጉ ፡ ?
ማን ፡ የእንግላንድ ፡ ንጉሥ ፡ ሆነ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፺፰ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ኖርማን ፡ የእንግሊዝ ፡ ንጉሥ ።

፩ ፤ አሸናፊው ፡ ዊልየም ፡ የተባለው፡የኖርማንዲ፡ዱክ ፡ የነበረው፡፳፡ዓመት፡ያህል ፡ ከነገሠ ፡ በኋላ ፡ ዊልየም ፡ ሩፉስ ፡ የተባለው፡ሁለተኛው ፡ ልጁ፡ዙፋኑን ፡ ወረሰ ። ይኸም ፡ የራሱ ፡ ጸጕር ፡ ቀይ ፡ ስለ፡ ነበረ ፡ ዊልየም ፡ ሩፉስ ፡ ወይም ፡ ዊልየም ፡ ቀዩ ፡ ይሉት ፡ ነበር ።

፪ ፤ ይህም ፡ ቀዩ ፡ ንጉሥ ፡ አደን ፡ ይወድ ፡ ነበር ። አንድ፡ቀን ፡ በደን ፡ ውስጥ ፡ ድኩላ ፤ አገኘና ፡ ሲያበርር ፡ አንድ ፡ ዋልተር ፡ ታየርድ፡የተባለ ፡ ሰው ፡ ቀስት ፡ ቢወረውር ፡ ፍላጻው ፡ ከዛፍ፡ ላይ ፡ ዳልጦ ፡ ሄዶ ፡ በንጉሡ ፡ ደረት ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተተከለ ፡ ያንጊዜውን ፡ ከፈረሱ ፡ ወደቀና ፡ ሞተ ።

፫ ፤ ይህም ፡ የሆነው፡በሺ፡፩፻ ፡ ዓመት ፡ ነው ። ከዊልየም፡ሩፉስ ፡ ቀጥሎ ፡ ሄንሪ፡ የተባለ ፡ የዊልየም ፡ ሩፉስ ፡ ወንድም፡ነገሠ ። ይህም፡ንጉሥ፡ቤንክለርክ፡ወይም፡

የከበረ ፡ ተማሪ ፡ ተባለ ። ምክንያቱም ፡ ስሙን ፡ መጻፍ ፡ ስለ፡ቻለ ፡ ነው ። በዚያን ፡ ዘመን ፡ ነገሥታት ፡ በጣም ፡ እንዲማሩ ፡ አይታሰብም ፡ ነበር ። ንጉሥ ፡ ሄንሪ፡ቤንክለርክ ፡ በሺ፡ ፩፻፴፭ ፡ ሲሞት ፡ ዙፋኑን ፡ እስጢፋኖስ ፡ የተባለ፡ዙፋን፡ የማይገባው፡ያዘው ። ወዲያው ፡ በሺ፡ ፩፻፶፬ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ሞተና ፡ የፊተኛው ፡ ሄንሪ፡ ልጅ ፡ ሄንሪ ፡ ሁለተኛ ፡ የተባለ ፡ ዙፋኑን ፡ ወረሰ ።

፪ ፤ ይህ ፡ ንጉሥ ፡ ቶማስ ፡ ቤኬት ፡ ከተባለው ፡ ተካንቴቡሪ ፡ ጳጳስ ፡ ጋር ፡ የመረረ ፡ ጸብ ፡ ነበረው ። ንጉሡን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ ብለው ፡ አራት ፡ ናይቶች ፡ ወደ ፡ ካንቴቡሪ ፡ ሄዱና ፡ ቤኬትን ፡ ከመሠዊያው ፡ ሥር ፡ አረዱት ። ነገር፡ግን፡ ጳጳሱ ፡ ሊገዝተው ፡ አስፈራርቶታልና ፡ ይህ ፡ ደም ፡ የመላበት ፡ ሥራ ፡ ለንጉሥ ፡ ሄንሪ ፡ ታላቅ ፡ መከራ ፡ ሊያመጣበት ፡ ሆነ ።

፫ ፤ ንጉሡ ፡ ተጳጳሱ ፡ ጋር ፡ ዕርቅ ፡ ለማድረግ ፡ ብሎ ፡ ቤኬት ፡ ወደ ፡ ተቀበረበት ፡ ገዳም ፡ ሄዶ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ መነኰሳቱ ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡ በሽመል ፡ እያገላበጡ ፡ አዋረዱት ። ንጉሡም ፡ ሳይከላከል ፡ በመገረፉ ፡ ስለ ፡ ትዕግሥቱ፡ ካሣ ፡ ከጳጳሱ ፡ ይቅርታ ፡ አገኘ ።

፬ ፤ በዚህ ፡ ንጉሥ ፡ ዘመን ፡ አየርላንድ ፡ ተሸነፈና፡ለእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ተጨመረ ። በፊት ፡ አያሎች ፡ የተለያዩ ፡ መንግሥታት ፡ ተብለው፡ተከፋፍለው፡ ነበር ።

፭ ፤ ሪካርድ ፡ ልበ ፡ አንበሳ ፡ የተባለ ፡ የእንግሊዝ፡ንጉሥ ፡ ተብሎ ፡ በሺ፡ ፩፻፹፱ ፡ ዘውድ ፡ ጫነ ። እርሱም ፡ ጨካኝና ፡ ኀይለኛ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ከመዋጋትና ፡ ከመጋደል ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ደስ ፡ አይለውም ፡ ነበር ። በጳለስቲና፡ታላቅ፡ ስምና ፡ ዝና ፡ አግኝቶ ፡ ሲመለስ ፡ የአውስትሪያ ፡ ዱክ ፡ በመንገድ ፡ አገኘውና፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ አሰረው ።

፮ ፤ ሪካርድ ፡ የሚፈታበት ፡ መንገድ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ በመስጠት ፡ ብቻ ፡ መሆኑን፡ እንግሊዝ ፡ ከዐወቀ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ ይህ ፡ ከሆነ ፡ በላይ ፡ ሳይቈይ ፡ የኖርማንዲ ፡ ከተማ ፡ በተከበበ ፡ ጊዜ ፡ ባሽጋጋሪ ፡ በፍላፃ ፡ ተወግቶ ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ ቀጥሎ ፡ ጆን ፡ የተባለ ፡ የሪካርድ ፡ ወንድም ፡ ነገሠ ። ሁለተኛው ፡ ስሙ ፡ ላክላንድ ፤ ወይም ፡ ሎስላንድ ፡ ይሉት ፡ ነበር ።

፯ ፤ የእንግሊዝ፡ነገሥታት ፡ ካሁን ፡ ቀደም ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ የያዙዋቸውን ፡ ግዛቶች ፡ በማጣታቸው ፡ ይህ ፡ ሹመት ፡ ለጆን ፡ ተሰጠ ። ከፉዎች ፡ ተብለው ፡ ተሚጠሩት ፡ ከእንግሊዝ ፡ ነገሥታት ፡ አንዱ ፡ የበለጠ ፡ ክፉ ፡ የሚባል ፡ ጆን ፡ ነበር ። ካደረጋቸው ፡ በደሎች ፡ አንዱን ፡ ዘውድ ፡ የሚገባውን ፡ የብሬታኝ ፡ አርቱር ፡ የተባለውን ፡ የእኅቱን ፡ ልጅ ፡ መግደሉ ፡ ነው ።

፰ ፤ የእንግሊዝ ፡ ባሮንስ ፡ ሁሉ ፡ የጆንን ፡ ዐመል ፡ ስለ ፡ ተጸየፉት ፡ ቡኒሜድ ፡ በሚሉት ፡ ስፍራ ፡ ተሰባሰቡና ፡ (ማግና ፡ ካርታ ፡ )ማነኛውም ፡ ጕዳይ ፡ በፊርማ ፡ እንዲደረግ ፡ በግድ ፡ አስፈረሙት ። ይህ ፡ የሥልጣን ፡ ጽሕፈት ፡ በሰኔ ፡ ፲፭ ፡

ቀን፡ሺ፡፪፻፲፭ ፡ ዓ. ም. ተደረገ ። ይህም ፡ የእንግሊዝ ፡ ነጻነት ፡ መሠረት ፡ ተብሎ ፡ ታሰበ ። የቀድሞ ፡ ነገሥታት ፡ እንደ፡ፈቀዳቸው ፡ የሚያደርጉበት ፡ ሥልጣን ፡ ለጆንና ፡ ለተከታዮቹ ፡ ጐደለባቸው ።

፲፩ ፡ በሺ፡፪፻፲፮ ፡ ጆን ፡ ሞተና ፡ ዘውዱን ፱ ፡ ዓመት ፡ ለሆነው ፡ ልጁ ፡ ተወለት ። እርሱም ፡ ሄንሪ ፡ ሦስተኛ ፡ ተብሎ ፡ ፶፮ ፡ ዓመት ፡ ገዛ ። ምንም ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ቢባል ፡ ለገዢነት ፡ የሚበቃ ፡ ጥበብና ፡ ኀይል ፡ አልነበረውም ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፡ በዊልየም ፡ አሸናፊ ፡ ዙፋን ፡ ማን ፡ ተቀመጠ ፡ ?

፪ ፡ ዊልየም ፡ ሩፉስ ፡ በመጨረሻው ፡ ምን ፡ ደረሰበት ፡ ?

፫ ፡ ሄንሪ ፡ ቤንክለርክ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነገሠ ፡ ? እስጢፋኖስ ፡ በዙፋን ፡ የተቀመጠው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ።
ምን ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ፡ ?

፬ ፡ ቶማስ ፡ በኬትን ፡ ማን ፡ ገደለው ፡ ?

፭ ፡ በሄንሪ ፡ ሁለተኛ ፡ ምን ፡ ደረሰበት ፡ ?

፮ ፡ አየርላንድ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፯ ፡ ሪካርድ ፡ የእንግላንድ ፡ ንጉሥ ፡ የሆነው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

፰ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ? እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? አሙዋሙዋቱ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
ስለምን ፡ ጆን ፡ ላክላንድ ፡ ተባለ ፡ ? እንደምን ፡ ሆነ ፡ ? ምን ፡ በደለ ፡ ?

፲ ፡ ማግና ፡ ካርታ ፡ የሚባለውን ፡ ውል ፡ የፈረመ ፡ ማነው ፡ ?

፲፩ ፡ ይህ ፡ እንደምን ፡ ይታሰባል ፡ ? ንጉሡ ፡ ጆን ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ፡ ? ሄንሪ ፫ኛ ፡ እንደምን ፡ ሆነ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፻፳፭ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፡ እንግሊዝ ፡ ጦርነትና ፡ ዐመፅ ።

፩ ፤ በሺ ፡ ፪፻፸፪ ፡ የነገሠውን፡ኤድዋርድ ፡ አንደኛ ፡ የተባለውን ፡ የእግሩ ፡ ቅል ጥም ፡ ያለመጠን ፡ ረጅም፡ስለ፡ነበረ ፡ ሕዝቡ ፡ በሐሜት ፡ ስም ፡ ሎንግሻንክስ፡ ይሉት ፡ ነበር ። እጅግ ፡ ጀግና ፡ ነበርና ፡ በጳለስቲናና ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ በተነሣው ፡ ጦርነት ፡ በጀግንነት ፡ ተዋግቶአል ።

፪ ፤ ካሁን ፡ ቀደም ፡ ለብቻው ፡ የተለየ ፡ መንግሥት ፡ የነበረውን ፡ ዌልስን ፡ ኤድዋ ርድ ፡ ተዋግቶ ፡ ድል ፡ አድርጎታል ። እንደዚሁ ፡ እስኮትላንድን፡መትቶ፡ድል ፡ ለማድረግ ፡ አዲቦለት ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የታወቀው ፡ ሰር፡ዊልየም ፡ ዋሌስ ፡ ስለ ፡ ተቋቋመው ፡ ገና ፡ አልተሳካለትም ፡ ነበር ። የእንግሊዝንም ፡ ጦር ፡ እየመላ ለሰ ፡ ተምትሞታል ። በመጨረሻው ፡ ዋሌስ ፡ ስለ ፡ ተያዘ ፡ በሰንሰለት ፡ አስረው ፡ ወደ ፡ ሎንዶን ፡ ወሰዱትና ፡ ተፈረደበት ።

፫ ፤ ሮበርት ፡ ብሩስ ፡ የተባለ ፡ የእስኮትላንድን ፡ ዘውድ ፡ ተፋልሞ ፡ በኤድዋርድ፡ ላይ ፡ ያለውን፡ጦርነት፡እንደ፡ገና፡አደሰው ። ነገር፡ግን ፡ ሎንግሻንክስ ፡ የያዘውን ፡ እስኮትላንድን ፡ ለመልቀቅ፡አሳብ ፡ አልነበረውምና ። ልክ ፡ የሌለው ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ወገን ፡ ሲጓዝ ፡ ባልታሰበ ፡ ሕመም ፡ ሕይወቱ ፡ አቋረጠ ።

፬ ፤ ኤድዋርድ ፡ ሁለተኛ ፡ የተባለ ፡ ልጁ ፡ በሺ ፡ ፫፻፯ ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀመጠና ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ወታደሮች ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ እስኮትላንድ ፡ ተጓዘ ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ ያለ ፡ አርበኛ ፡ አልነበረም ። ቢሆንም ፡ ሮበርት ፡ ብሩስ ፡ ፴ ፡ ሺሕ ፡ ጦር ፡ ብቻ ፡ ይዞ ፡ ስለ ፡ ገጠመው ፡ የተመሰገነ ፡ ድል ፡ አገኘና ፡ እስኮትላንድን ፡ ነጻ ፡ አወጣት ። ኤድዋርድ ፡ ሁለተኛም ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ነገሠ ። እርሱ ፡ ሰነፍና ፡ የሚያ ሳዝን ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ። የገዛ ፡ ሚስቱ ፡ ተዋግታ ፡ ድል ፡ አደረገችውና ፡ አሰ ረችው ። ወዲያው ፡ አጣድፋ ፡ በእስር ፡ ቤት ፡ ሳለ ፡ አሳረደችው ።

፭ ፤ ልጁ ፡ ኤድዋርድ ፡ ፫ኛ ፡ በተወለደ ፡ በ፲፭ ፡ ዓመቱ ፡ በሺ ፡ ፫፻፳፯ ፡ መንገሥ ጀመረ ። ከባቱ ፡ በጣም ፡ ልዩነት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ ሳያሳይ ፡ በዙፋኑ ፡ አልተቀመጠም ። ሆሊዶን ፡ በምትባል ፡ ኮረብታ ፡ እስኮትላንዶችን ፡ መታ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ፈረንሳይን ፡ ወረረ ። በፈረንሳይ ፡ ታሪክ ፡ ስለ ፡ ፈረንሳይ ፡ ጦርነት ፡ ተናግሬያለሁ ።

፮ ፤ የሞጋሳ ፡ ስሙ ፡ ጥቍር ፡ ፕሪንስ ፡ የተባለው ፡ የንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ከባቱ ፡ የበ ለጠ ፡ ጀግና ፡ ነበር ። ጀግና ፡ ሳለ ፡ ደግሞ ፡ ቸር ፡ ሰው ፡ ነበር ። የፈረንሳይን ፡ ንጉሥ ፡ ጆንን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ በማረከው ፡ ጊዜ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ደስታ ፡ አላ ደረገም ። አንድነት ፡ ሁነው ፡ ሎንዶን ፡ ሲገቡ ፡ ጥቍር ፡ ፕሪንስ ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ አን ዳች ፡ ሳያደርግ ፡ በዶ ፡ ራሱን ፡ ሆኖ ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡ ሳይመስል ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ዘበኛ ፡ መስሎ ፡ በተማረከው ፡ ንጉሥ ፡ አጠገብ ፡ ይጋልብ ፡ ነበር ።

፯ ፤ ይህ ፡ ጀግና ፡ ፕሪንስ ፡ በሺ ፡ ፫፻፸፮ ፡ ሞተ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አባቱ ፡ የቈየው ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ቀጥሎ ፡ የነገሠው ፡ ሪካርድ ፡ ሁለተኛ ፡ የተባለ ፡ የ፲፩ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበር ። ሪካርድም ፡ ባደገ ፡ ጊዜ ፡ የመንግሥቱን ፡ ጕዳይ ፡ ቻል ፡ ብሎ ፡ የራሱን ፡ ደስታ ፡ ብቻ ፡ ከመፈለግ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አሳብ ፡ አልነበረውም ።

፰ ፤ በዘመኑ ፡ ዋት ፡ ታይለር ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ብረት ፡ ቀጥቃጭ ፡ ዋና ፡ ሁኖ ፡ ሕዝቡን ፡ አሳደመበት ። ደግሞ ፡ በዚሁ ፡ ዐመፅ ፡ ውስጥ ፡ ዋኖች ፡ የሆኑ ፡ ጃክእ ስትሮና ፡ ሆብ ፡ ካርተር ፡ የተባሉ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። መቶ ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ሎንዶን ፡ ተጓዙና ፡ ብዙ ፡ ጥፋት ፡ አደረጉ ።

፱ ፤ ንጉሡም ፡ ጉባኤ ፡ አድርጎ ፡ ለመመካከር ፡ አሰበና ፡ ጥቂቶች ፡ መኳንቶችን ፡ አስከትሎ ፡ ወደ ፡ ዋት ፡ ታይለር ፡ ቢሄድ ፡ ይኸው ፡ ቀጥቃጭ ፡ ባለጌ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ንጉሡን ፡ እንደ ፡ ማንም ፡ እንደ ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ ቈጠረውና ፡ የሚገባውን ፡ ከበ ሬታ ፡ ሳያደርግለት ፡ እንዲያውም ፡ ሰይፉን ፡ መዘዘና ፡ ንጉሡን ፡ ገላመጠው ።

፲ ፤ ዊልየም ፡ ዋልዎርት ፡ የተባለ ፡ የሎንዶን ፡ ሎርድ ፡ ሜጄር ፡ በንጉሡ ፡ አጠ ገብ ፡ ቁሞ ፡ ነበርና ፡ ዋት ፡ ታይለር ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ያሳየውን ፡ ትዕቢት ፡ በተ መለከተ ፡ ጊዜ ፡ ተቈጣና ፡ ታላቅ ፡ ዱላ ፡ አንሥቶ ፡ ዋት ፡ ታይለርን ፡ መታው ። ወዲያው ፡ ቀጥሎ ፡ አንዱ ፡ ሹም ፡ በሰይፍ ፡ ጨረሰው ።

፲፩ ፤ ዐምፀው ፡ የነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ ጀግናው ፡ ብረት ፡ ቀጥቃጭ ፡ ተደብድቦ ፡ መሞ ቱን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ተናደዱና ፡ በንጉሡ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ለመነሣት ፡ ፈልገው ፡ ተጨዋጨዋኹ ። ንጉሥ ፡ ሪካርድ ፡ ግን ፡ በድፍረት ፡ ወደነሱ ፡ ሄደና ፡ በእጁ ፡ እየጠቀሰ ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ ጮኸ ።

፲፪ ፤ መሪያችሁ ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ አትዘኑ ! ከዋት ፡ ታይለር ፡ ይልቅ ፡ የኔ ፡ የንጉሣ ችሁ ፡ መሪነት ፡ ይሻላችኋል ፡ ›ቢላቸው ፡ የንጉሡ ፡ ቃል ፡ ተደመጠለትና ፡ ያመፀው ፡ ሕዝብ ፡ ያን ፡ ጊዜውን ፡ ለንጉሡ ፡ ታዘዘለት ፡ እንጂ ፡ የዋት ፡ ታይለርን ፡ ደም ፡ አንድም ፡ የተበቀለው ፡ አልተገኘም ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ኤድዋርድ ፡ ፩ኛ ፡ ዘውድ ፡ የጫነው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
ሕዝቡ ፡ ማን ፡ ብለው ፡ ሰየሙት ፡ ? ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፪ ፤ ዌልስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ኤድዋርድን ፡ በእስኮትላንድ ፡ የተከላከለው ፡ ማነው ፡ ? ዌሏየም ፡ ዋሌስ ፡ በመጨረሻው ፡ ምን ፡ ደረሰበት ፡ ?

፫ ፤ ሮበርት ፡ ብሩስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? የቅልጥመ ፡ ረጅሙ ፡ ሞት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፬ ፤ ኤድዋርድ ፡ ሁለተኛ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ? የባኖክበርን ፡ ውጊት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? እንደምን ፡ አድርጎ ፡ እስኮትላንድ ነጻ ፡ ወጣ ፡ ? ፡ በኤድዋርድ ፡ ፪ኛ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ደረሰበት ፡ ?

፭ ፤ ኤድዋርድ ፡ ፫ኛ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ? መንገሥ ፡ የጀመረው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? ጥቍር ፡ ፕሪንስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፮ ፤ የፈረንሳይ ፡ ጆን ፡ የተባለ ፡ ምርኮኛውን ፡ እንደምን ፡ አኖረው ፡ ?

፯—፱ ፤ ሪካርድ ፡ ፪ኛ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ሽፍቶ ፡ የነበረው ዋት ፡ ታይለር ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፲ ፤ ዊልየም ፡ ዋልዎርት ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፲፩ ፤ ዋት ፡ ታይለር ፡ ከተገደለ ፡ በኋላ ፡ ዐመፁ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ሪካርድ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፻፳፮ ፡ ኢውሮጳ ።

### ስለ ፡ እንግሊዝ ፡ ላንካስትሪያን ፡ ነገሥታት ።

፩ ፤ ላመፀኛው ፡ ሕዝብ ፡ ምንም ፡ የሰጠውን ፡ ተስፋ ፡ ባያስቀር ፡ ንጉሥ ፡ ሄንሪ ፡ መልካም ፡ ገዢ ፡ አልነበረም ። ዜጎቹ ፡ እያደር ፡ እየከፋቸው ፡ ያንጐረጕሩ ፡ ነበሩ ። ሪካርድንም ፡ ተዙፋኑ ፡ አወረዱና ፡ በፓንቴፍራክ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አሰሩት ። በዚያ ፡ ሳለ ፡ ገደሉት ፤ ወይም ፡ በረኃብ ፡ ሞተ ፡ ይባላል ። በሺ ፡ ፬፻ ፡ —የላንካስትር ፡ ዱክ ፡ የነበረው ፡ አጐቱ ፡ አስቀድሞም ፡ መንግሥቱን ፡ ሊወስድበት ፡ አስቦ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ነገሠና ፡ ሄንሪ ፡ ፬ኛ ፡ ተብሎ ፡ ተሠየመ ።

፪ ፤ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ የተነሡ ፡ ዐመፀኞች ፡ ከሁለት ፡ ወገን ፡ ነበሩ ። ፩ዱ ፡ የኖርተምበር ፡ ኤርል ፡ ነው ፤ ፪ኛው ፡ የዮርክ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ነው ። በዚያን ፡ ዘመን ፡ የነበሩ ፡ ጳጳሳት ፡ የጦር ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ የወታደርነት ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ ነበር ። ሄንሪ ፡ የተነሡበትን ፡ ዐመፀኞች ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ብዙ ፡ ዓመት ፡ በሰላም ፡ ገዛ ።

፫ ፤ የንጉሡ ፡ የበኵር ፡ ልጅ ፡ አባቱ ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ ያልተገራና ፡ ስድ ፡ እንደፈቃዱ ፡ የተለቀቀ ፡ ልጅ ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ አባቱ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ጠባዩ ፡ ተለወጠና ፡ ብልግናውን ፡ ትቶ ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የታጠቀ ፡ ሆነ ። በሺ ፡ ፬፻፲፫ ፡ ነገሠና ፡ ሄንሪ ፡ ፭ኛ ፡ ለመባል ፡ በቃ ። በነገሠ ፡ በ፪ኛው ፡ ዓመት ፡ ፈረንሳይን ፡ ወረረ ።

፬ ፤ ስመ ፡ ጥሩ ፡ በሆነው ፡ በአጂንኮርት ፡ ውጊያ ፡ ጊዜ ፡ ሄንሪ ፡ ፈረንሳይን ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ወጋውና ፡ ድል ፡ እንዳደረገው ፤ በኋላም ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ መላውን ፡ የፈረንሳይን ፡ መንግሥት ፡ ጠቅልሎ ፡ እንደ ፡ ገዛው ፤ ስለ ፡ ፈረንሳይ ፡ ስተርክ ፡ ነግሬያችኋለሁ ፤ ዕድሜው ፤ ፴፬ ፡ ዓመት ፡ ሲሆን ፡ በሺ ፡ ፬፻፳፪ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ሲገባ ፡ ሕይወቱ ፡ አቋረጠ ።

፭ ፤ አዲሱ ፡ የእንግሊዝ ፡ ንጉሥ ፡ ሄንሪ ፡ ፮ኛ ፤ የ፱ ፡ ወር ፡ ሕፃን ፡ ነበር ። ለጋው ፡ ሕፃን ፡ ገና ፡ በሞግዚቱ ፡ ክንድ ፡ ሳለ ፡ ከባዳው ፡ የእንግሊዝና ፡ የፈረንሳይ ፡ ዘውድ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ተጫነበት ። የዚህ ፡ የሚያሳዝን ፡ ሕፃን ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡

በፓሪስ ፡ ከተማ ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ወዲያው ፡ የፈረንሳይ ፡ ዘውድ ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ ሄደበት ። የእንግሊዙ ፡ ግን ፡ ለርሱ ፡ እንደ ፡ ሥቃይ ፡ ሆኖበት ፡ በሕይወቱ ፡ አለ ፡ ድረስ ፡ አብሮት ፡ ቈየና ፡ በመጨረሻው ፡ የሞቱ ፡ ምክንያት ፡ ሆነ ።

፮ ፡ ባደገ ፡ ጊዜ ፡ ፍጹም ፡ የዋህ ፡ ሰው ፡ ወጣው ። እንደ ፡ ንጉሥ ፡ የሚታይ ፡ ሳይሆን ፡ የተናቀና ፡ አንድ ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ የሚመስል ፡ ሆነ ። ከርሱ ፡ ይልቅ ፡ ሚስቱ ፡ ወንዳወድ ፡ ስለ ፡ ነበረች ፡ እርሱን ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ አድርጋ ፡ ትገዛው ፡ ነበር ።

፯ ፡ በዚሁ ፡ ንጉሥ ፡ ዘመን ፡ ያበባ ፡ ዘመቻ ፡ የሚሉት ፡ ተነሣ ። እዚህ ፡ ላይ ፡ እን ባቢዎች ፡ ልብ ፡ ታደርጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የላንካስትር ፡ ዱክ ፡ ከሪካርድ ፡ ሁለተኛ ፡ ላይ ፡ ቀምቶ ፡ በማይገባ ፡ ዘውዱን ፡ ወስዶበት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እርሱና ፡ ልጁ ፡ ጦረኞች ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ በሰይፋቸው ፡ እየተከላከሉ ፡ እምብዛም ፡ ሳይነቀፉ ፡ ዘውዱን ፡ እንደያዙ ፡ ቈዩ ።

፰ ፡ ሄንሪ ፡ ፮ኛ ፡ ልስልስ ፡ የዋህ ፡ ገር ፡ ሰላማዊ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ አባቱ ፡ የተ ወውን ፡ ዘውድ ፡ ተዋግቶ ፡ ለማስመለስ ፡ የሚበቃ ፡ ወኔ ፡ አልነበረውም ። ስለ ዚህ ፡ የሁለተኛ ፡ ሪካርድ ፡ ወራሾች ፡ የሚገባቸውን ፡ ርስት ፡ ለማስመለስ ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ ፈለጉ ። ለዚህም ፡ የሚቀርብ የዮርክ ፡ ዱክ ስለ ፡ ነበረ ፡ በ፲፻፬፻፶፭ ፡ ጦር ነት ፡ ጀመረ ። ከሄንሪ ፡ ፮ኛ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ተቃዋሚ ፡ ባይኖር ፡ ዘውዱን ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ይቀማው ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ማርጋሬት ፡ የተባለች ፡ የሄንሪ ፡ ሚስትና ፡ ሌሎችም ፡ መኳንንት ፡ ለንጉሡ ፡ ረዳት ፡ ሆነው ፡ ለመዋጋት ፡ ሲታጠቁ ፡ ሌሎች ፡ መኳንንቶች ፡ ግን ፡ ለዮርክ ፡ ዱክ ፡ ረዳት ፡ ሰደዱ ።

፱ ፡ መላው ፡ የዮርክ ፡ ሕዝብና ፡ የዮርክ ፡ ዱክ ፡ ወገኖች ፡ የሆኑ ፡ ሁሉ ፡ በደረ ታቸው ፡ ወይም ፡ በባርኔጣቸው ፡ ላይ ፡ ነጭ ፡ አበባ ፡ አደረጉ ። ደግሞ ፡ ላንካስ ቲሪያን ፡ ወይም ፡ የንጉሥ ፡ ወገን ፡ የሆኑት ፡ ሁሉ ፡ ቀይ ፡ አበባ ፡ አደረጉ ። መቸ ውንም ፡ ሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ነጭ ፡ አበባ ፡ ያደረገ ፡ ሁለተኛው ፡ ቀይ ፡ አበባ ፡ ያደረገ ፡ በተገናኙ ፡ ጊዜ ፡ ሰይፋቸውን ፡ መዝዘው ፡ ይዋጉ ፡ ነበር ። እንደዚህ ፡ አድ ርገው ፡ የእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ ከሁለት ፡ ተከፍለው ፡ ቀይ ፡ ወይም ፡ ነጭ ፡ አበባ ፡ በማድረግ ፡ ልዩነት ፡ እንዲያው ፡ አንገት ፡ ላንገት ፡ ተያይዘው ፡ ይተራረዱ ፡ ነበር ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፡ ሪካርድ ፡ ይገዛ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ እንግላንድ ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ?
ከዙፋን ፡ ያወረደው ፡ ማነው ፡ ? ምን ፡ ደረሰበት ፡ ? ፬ኛ ፡ ሄንሪ ፡ የተባለ ፡
ማነው ፡ ?
ምን ፡ ጊዜ ፡ መንገሥ ፡ ጀመረ ?

፪ ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ያመፁበት ፡ እነማን ፡ ናቸው ፡ ?

፫ ፡ ሄንሪ ፡ ፭ኛ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ? ፈረንሳይን ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ወረረው ፡ ?

፬ ፡ በአጂንኮርት ፡ የተዋጋ ፡ ማነው ፡ ? ሄንሪ ፡ ፭ኛ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ፡ ?

፭ ፤ ስለ ፡ ሄንሪ ፡ ፮ኛ ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ተናገር ።
፮ ፤ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ ? ሚስቱ ፡ እንዴት ፡ ያለች ፡ ናት ፡ ?
፯ ፤ የላንካስትር ፡ ዱክ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ? ልጁ ፡ ሄንሪ ፡ ፬ኛ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?
፰-፱ ፤ የሪካርድ ፡ ፪ኛ ፡ ወራሾች ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ? የዮርክ ፡ ዱክ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ጦርነት ፡ ጀመረ ፡ ? ስለ ፡ ሄንሪ ፡ ብሎ ፡ መሣሪያ ፡ ያነሣ ፡ ማነው ፡ ?
፲ ፤ የዮርክ ፡ ዱክ ፡ ተከታዮች ፡ የለበሱት ፡ ምንድነው ፡ ? የንጉሡ ፡ ተከታዮችስ ፡ ? ሁልጊዜ ፡ የሚሆነው ፡ ምንድነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፻፳፯ ፡ ኤውሮጳ ፡ ።

### ስለ ፡ አበቦች ፡ ጦርነት ።

፩ ፤ ያበቦች ፡ ጦርነት ፡ እስከ ፡ ፴ ፡ ዓመት ፡ ቈየ ፤ አንዳድ ፡ ጊዜ ፡ ባለነጭ ፡ አበባዎች ፡ የበላይ ፡ ሲሆኑ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ባላቀይ ፡ አበባዎች ፡ ገልብጠው ፡ የበላይ ፡ ይሆኑ ፡ ነበሩ ። በዚህ ፡ ጦርነት ፡ የታወቀ ፡ ጀኔራል ፡ የነበረ ፡ የዋርዊክ ፡ ኤርል ፡ ነበር ፤ መቸውንም ፡ በሱ ፡ ወገን ፡ ያሉት ፡ ባለነጭ ፡ አበባ ፡ ወታደሮች ፡ እየመላለሱ ፡ ቶትን ፡ በሚባል ፡ ስፍራ ፡ ድል ፡ አድርገዋል ። በዚህ ፡ ጦርነት ፡ ከባለቀይ ፡ አበባዎች ፡ ወታደሮች ፡ ወገን ፡ ፴፮ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ተገድለዋል ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ ስሙን ፡ ኤድዋርድ ፡ አራተኛ ፡ አሰኝቶ ፡ የዮርክ ፡ ዱክ ፡ ነገሠ ።
፪ ፤ ይህም ፡ የሆነው ፡ በሺ ፡ ፬፻፷፩ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ሳይቈይ ፡ የዋርዊክ ፡ ኤርል ፡ ከንጉሥ ፡ ኤድዋርድ ፡ ጋር ፡ ተጣላና ፡ የዮርክን ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ዝም ፡ አሰኛቸው ። ሄንሪ ፡ ፮ኛን ፡ ከታሰረበት ፡ ፈታና ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ዙፋኑ ፡ ስለ ፡ አስቀመጠው ፤ ኤድዋርድም ፡ ወደ ፡ ፈረንሳይ ፡ አገር ፡ እንዲሸሽ ፡ ግድ ፡ ሆነበት ።
፫ ፤ የዋርዊክ ፡ ኤርል ፡ ነገሥታትን ፡ ከዙፋናቸው ፡ ዘርጥጦ ፡ ለማውረድና ፡ ሌሎችን ፡ በዙፋን ፡ ለማስቀመጥ ፡ ችሎት ፡ ያለው ፡ ኀይለኛ ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ አሳየ ፡ ንጉሥ ፡ አድራጊው ፡ የመባል ፡ ስም ፡ አገኘ ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ላንካስትሪያን ፡ በጀግንነት ፡ ሲዋጋ ፡ በመጨረሻው ፡ ከጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ ባለነጭ ፡ አበባዎች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ገኑ ።
፬ ፤ በሺ ፡ ፬፻፹፫ ፡ ፭ኛ ፡ ሄንሪ ፡ ከነልጁ ፡ ስለ ፡ ተገደለ ፡ ኤድዋርድ ፡ ፬ኛ ፡ ተከራካሪ ፡ የሌለው ፡ የእንግሊዝ ፡ ንጉሥ ፡ ሆነ ። ስለ ፡ አልጋው ፡ በጀግንነት ፡ ተዋግቶ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ መንግሥቱ ፡ ተደላድሎለትና ፡ ጸንቶለት ፡ ሳለ ፤ ሰነፈና ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ወዳጅ ፡ ሆነ ።
፭ ፤ ደግሞም ፡ ግፈኛ ፡ ገዢ ፡ ሆነ ። ከወንድሞቹ ፡ አንዱን ፡ ለመግደል ፡ አስቦ ፡ የትኛውን ፡ አሟሟት ፡ እንደሚመርጥ ፡ ፈቀደለት ። ወንድሙም ፡ አጥብቆ ፡ የሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ ይወድ ፡ ነበርና ፡ ወይን ፡ በተመላበት ፡ በርሚል ፡ ሰጥሞ ፡ መሞትን ፡ መረጠ ።

፮ ፤ ፬ኛ ፡ ኤድዋርድ ፡ በ፲፬፻፹፫ ፡ ሞተ ። ሁለት ፡ ሕፃናት ፡ ልጆች ፡ ትቶ ፡ ነበርና ፡ ታላቁ ፡ በኋላ ፡ ንጉሥ ፡ ኤድዋርድ ፡ ፭ኛ ፡ የተባለው ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ለነዚህ ፡ ለሚያሳዝኑ ፡ ሕፃናት ፡ እንደ ፡ ጠባቂ ፡ የነበረ ፡ የግሎስትር ፡ ዱክ ፡ ሪካርድ ፡ የተ ባለ ፡ አጐት ፡ ነበራቸው ። እያሎች ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ እንደሚሉት ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ለማየት ፡ የሚያስፈራ ፡ ከትከሻው ፡ ጉብር ፡ የነበረው ፡ ክንዱ ፡ የደረቀ መልክ ፡ ጥፉ ፡ ነበር ፡ ይላሉ ። የዛሬው ፡ ዘመን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ሲጽፉ ፡ ግን ፡ ጀግና ፡ ብልህ ፡ አሳቡን ፡ ለመፈጸም ፡ የቈረጠ ፡ ወደ ፡ አሰበው ፡ ለመድረስ ፡ የማይጠ ራጠር ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ ብለው ፡ ይጽፋሉ ። ይህም ፡ ሰው ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ እንዲ ነግሥ ፡ ቊርጥ አሳብ ፡ ነበረው ።

፯ ፤ ትንሹ ፡ ንጉሥ ፡ ኤድዋርድና ፡ ወንድሙ ፡ በሎንዶን ፡ ግንብ ፡ ውስጥ ፡ እንዲጠበቁ ፡ አደረገ ። አንድ ፡ ቀን ፡ ሌሊት ፡ እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ሕፃናት ፡ ተቃቅፈው ተኝተው ፡ የጠለቀ ፡ እንቅልፍ ፡ ወስዶአቸው ፡ ሳሉ ፡ አንድ ፡ ጨካኝ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ትራስ ፡ አንሥቶ ፡ ሚነባቸውና ፡ ታፍነው ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ከዚያው ፡ ከደረጃ ፡ ሥር ፡ ተቀበሩ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የግሎስትር ፡ ዱክ ፡ የነበረው ፡ ሪካርድ ፡ የእ ንግሊዝ ፡ ንጉሥ ፡ ሆነ ። ዘውዱን ፡ ለማግኘት ፡ ብሎ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ሠርቶ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ መንግሥቱ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አልቈየለትም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በድራጊው ፡ ላይ ፡ እንደሚደርስ ፡ ታውቆዋል ።

፰ ፤ የንጉሥ ፡ ሄንሪ ፡ ፯ኛውን ፡ ዘውድ ፡ የሚወርስ ፡ የሪችሞንድ ፡ ኤርል ፡ ሄንሪ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ወጣት ፡ ብቻ ፡ ቀርቶ ፡ ነበር ። ሪካርድን ፡ ባለጉብሩን ፡ እንዲ ወጋ ፡ ፈረንሳዎች ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መሣሪያ ፡ ስለ ፡ ሰጡት ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ተሻግሮ ፡ በስዎርት ፡ በሚባል ፡ ስፍራ ፡ ተዋግቶ ፡ ድል ፡ አደረገው ።

፱ ፤ የሪችሞንድ ፡ ወታደሮች ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ የተከመረውን ፡ የሰው ፡ ሬሳ ሲያገላብጡና ፡ ሲመረምሩ ፡ የወርቅ ፡ ዘወ ዱን ፡ እንዳደረገ ፡ በዚያ ፡ መኻከል ፡ ንጉሥ ፡ ሪካርድን ፡ አገኙት ። ዘውዱን ፡ ወስደው ፡ በሪችሞንድ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ አደረጉና ፡ «ንጉሥ ፡ ሄንሪ ፡ ፯ኛ ፡ የተባልኸው ፡ አንተ ፡ ነህ ፡» ብለው ፡ እየጮኹ ፡ ለንጉሥ ፡ የተገባውን ፡ ሰላምታ ፡ አቀረቡለት ።

፲ ፤ አዲሱም ፡ ንጉሥ ፡ የኤድዋርድ ፡ አራተኛን ፡ ልጅ ፡ አገባ ። በሰርጋቸው ፡ ጊዜ ፡ እያንዳንዱ ፡ ነጭ ፡ አበባ ፡ እየተሰበጠረ ፡ የተቀላቀለበት ፡ የተጌጠ ፡ ቀይ ፡ አበባ ፡ ስለ ፡ ለበሱ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያበባ ፡ ጦርነት ፡ የሚሉት ፡ ቀረ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ያበባ ፡ ጦርነት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ቈየ ፡ ? የኤርል ፡ ዋርዊክ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፪ ፤ ኤድዋርድ ፡ አራተኛ ፡ የነገሠው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? ዋርዊክ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፫ ፤ ማን ፡ ይባል ፡ ነበር ፡ ? አሟሟቱ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ንጭ ፡ አበባ የተባሉት ፡ ወገኖች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ኀይል ፡ ያገኙት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
፬ ፤ ኤድዋርድ ፡ አራተኛ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?
፭ ፤ ወንድሙን ፡ እንዴት ፡ አደረገው ፡ ?
፮ ፤ ምን ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ፡ ? እንዴት ፡ ያሉ ፡ ልጆች ፡ ትቶ ፡ ነበር ፡ ? ስለጉ ባጣው ፡ ሪካርድ ፡ ተናገር ።
፯ ፤ እንዴት ፡ ያለ ፡ የአውሬነት ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ ኖሮአል ፡ ? ነግሦ ፡ ኖሮአልወይ ፡ ?
፰ ፤ በስምርት ፡ ላይ ፡ በተዋጉ ፡ ጊዜ ፡ ማን ፡ ድል ፡ አደረገ ፡ ?
፱ ፤ ሪካርድ ፡ የተገኘው ፡ ከወዴት ፡ ነው ፡ ?
፲ ፤ ፯ኛ ፡ ሄንሪ ፡ ለሚስትነት ፡ ማንን ፡ አገባ ፡ ? ያበባ ፡ ጦርነት ፡ ስለ ምን ፡ አለቀ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፰ ፡ ኤውሮጳ ።

### በስ ፡ ተደር ፡ ፕሪንሶች ፡ መንግሥ ።

፩ ፤ ሄንሪ ፡ ፯ኛ ፡ ( የቀድሞ ፡ የሪችሞንድ ፡ ኤርል ፡ ) በሺ ፡ ፬፻፹፭ ፡ ነገሠ ። ለሕዝቡ ፡ ደስታ ፡ የሚሆን ፡ ከማሰብ ፡ ይልቅ ፡ ለራሱ ፡ ሀብትና ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ የሚጠነቀቅ ፡ ብልጥ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ። ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ ሲል ፡ ከሌላ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ሳይጋጭ ፡ በገሩም ፡ ውስጥ ፡ ሁከት ፡ ሳይነሣ ፡ በሰላም ፡ መኖ ርን ፡ ፈለገ ።
፪ ፤ በዘመኑ ፡ ሁለት ፡ አታላዮች ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ተነሡ ። ሁሉም ፡ እያን ዳንዱ ፡ ተነሥተው ፡ ተሄንሪ ፡ ፯ኛ ፡ ይልቅ ፡ ዘውድ ፡ የሚገባው ፡ ለኔ ፡ ነው ፡ አሉ ። አንዱ ፡ ላምብር ፡ ሲምነል ፡ የተባለ ፡ የፋርኖ ፡ ጋጋሪ ፡ ልጅ ፡ ነው ። እርሱ ፡ ግን ፡ ራሱን ፡ የ፬ኛ ፡ ኤድዋርድ ፡ የወንድም ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ ይላል ። ሁለተኛው ፡ ፒርሲን ፡ ዋርበክ ፡ ይባላል ። እርሱም ፡ የሉክንዳ ፡ አራጅ ፡ ልጅ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሪካርድ ፡ በሎንዶን ፡ ግንብ ፡ አግብቶ ፡ ከፈናቸው ፡ ሕፃ ናት ፡ አንዱ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አለ ።
፫ ፤ አያሎች ፡ የእንግሊዝ ፡ ሹማምትና ፡ ከቡራን ፡ በነዚህ ፡ በሁለቱ ፡ አታላ ዮች ፡ ተመርተው ፡ ወደ ፡ ሽፍትነት ፡ አዘነበሉ ። በመጨረሻው ፡ ሁለቱም ፡ አታ ላዮች ፡ ተይዘው ፡ ከታሰሩ ፡ በኋላ ፡ ፐርኪን ፡ ዋርበክ ፡ ተሰቀለ ። ሊምበርት ሲምነል ፡ ለንጉሥ ፡ ወጥ ፡ ቤት ፡ ማህን ፡ አጣቢነት ፡ ገባ ።
፬ ፤ ሄንሪ ፡ ፯ኛ ፡ በሺ ፡ ፭፻፱ ፡ ሞተ ። እጅግ ፡ አድርጎ ፡ የገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ ያደረበት ፡ ሰው ፡ ነበርና ፡ እጁ ፡ የገባውን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ከረጅው ፡ ያገባ ፡ ነበር ። ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ዐሥር ፡ ሚሊዮን ፡ ፓውንድ ፡ እስተርሊንግ ፡ ተገኘ ።